# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሣይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

### የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

### ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በመምህራንና በተማሪዎች ላይ ያለው ተፅዕኖ ፍተሻ

### (በቸሃ ወረዳ አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)

በ

ማናስብ ታከለ

ጥቅምት፣2014 ዓ.ም

ጅማ፣ኢትዮጵያ

# የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በመምህራንና በተማሪዎች ላይ ያለው ተፅዕኖ ፍተሻ

## (በቸሃ ወረዳ አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)


ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሣይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል


ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ- ዘዴ ለሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ


ማናስብ ታከለ

ዋና አማካሪ፦ ምህረት ሳዳም (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ፡- ይክበር ይመስገን (M.A)



ጥቅምት፤2014 ዓ.ም

ጅማ፤ኢትዮጵያ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በመምህራንና በተማሪዎች ላይ ያለው ተፅዕኖ ፍተሻ (በቾሃ ወረዳ በተመረጡ አራት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)በሚል ርዕስ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነ-ዘዴ በሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት በማናስብ ታከለ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርስቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታገኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ---------- ፊርማ--------- ቀን---------

ፈታኝ ----------- ፊርማ-------- ቀን--------

ፈታኝ----------- ፊርማ--------- ቀን---------

## ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ፊርማየን ያስቀመጥኩት የድህረ ምረቃ ተማሪ ስሆን ይህ ጥናት የራሴ ስራ ስለመሆኑና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ፅሁፎችና መጽሀፍት ምንጮች በሙሉና በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ----------------------------------

ፊርማ ------------------------------

ቀን -----------------------------------

## ምስጋና

በመጀመሪያ አስጀምሮ ለዚህ ላደረሰኝ ለልዑል እግዚአብሔር ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን፡፡በመቀጠል ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠት፣ ስህተቴን በማረም ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ሳይሰስቱ ጥናቱ ትክክለኛውን አቅጣጫ እንዲይዝ ላደረጉልኝ ለአማካሪዎቼ ለዶ/ር ምህረት ሳዳም እና ለይክበር ይመስገን (MA) ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ እንዲሁም የተለያዩ መረጃዎችን በመስጠት ድጋፍ ላደረጉልኝ ለዶ/ር አገኘሁ ተስፋ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በመጨረሻም የጽሁፍ መጠይቁን ፣የቃለ መጠይቅ መረጃ በመስጠት ትብብር ላደረጉልኝ የጥናቱ ተሳታፊ መምህራንና ተማሪዎች ሁሉ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ  ትምህርቱን እንድማር እድሉን ላመቻቸልኝ ለጅማ ዩኒቨርስቲ፣ትምህርቱን ለሰጡኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ መምህራን ለቸሃ ወረዳ ትምህርት ጽህፈት ቤት በሙሉ ከፍ ያለ ምስጋና ይድረሳቸው፡፡

## አጠቃሎ

*የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ አብይ ዓላማ በቸሃ ወረዳ የሚገኙ በተመረጡ አራት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በተማሪዎችና በመምህራን ላይ ያለው ወሽባክ መፈተሽ ነው ፡፡ይህን ዓላማ ዳር ለማድረስ ጥናቱ ገላጭ የምርምር አይነትን የተጠቀመ ሲሆን ተግባራዊ የተደረገውም በቸሃ ወረዳ  አራት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆን የተመረጡት አመች ንሞና ዘዴን በመከተል ነው፡፡ በነእዚህ ትምህርት ቤቶች አምስት 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን በጠቅላይ ንሞና ተመርጠዋል፡፡ እንዲሁም 62 ተማሪዎች በቀላል ዕጣ ንሞና የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ የጥናቱ መረጃዎችም በጽሁፍ መጠይቅ ፣በቃለ መጠይቅ፣ በሰነድ ፍተሻና በክፍል ውስጥ ምልከታ ተሰብስበዋል፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎችም የጽሁፍ መጠይቁና በሰነድ ፍተሻ የተገኙት በመቶኛ ፣በቃለ መጠይቅና በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኑት ደግሞ ከአላማዎቹ አንፃር በእየጭብጣቸው አይነታዊ በሆነ መልክ ተተንትነዋል፡፡ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተውም ክልላዊ ፈተናው በተማሪዎች መማር ክንውን ላይ አወንታዊም አሉታዊም ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ይኸውም የክልላዊ ፈተናው በምርጫ መልክ መቅረቡ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማሻሻል የማያግዳቸው መሆኑ በተማሪዎች የመማር ስልት ላይ አወንታዊ ወሽባክ ፈጥሯል፡፡ እንዲሁም ክልላዊ ፈተናው ትኩረት በሚያደርግባቸው ይዘቶች ላይ ትኩረት ሰጥተው እንደሚያነቡና ከክሂሎች ይልቅ ለሰዋሰዋዊ ይዘቶች ትኩረት ሰጥተው የሚከታተሉ መሆኑ፣ከክልላዊ ፈተናው ጋር ግንኙነት ካላቸው ሰነዶች ማለትም ከአጋዥ መጽሀፈት፣ከቀደሙ አመታት የፈተና ሽቶች የሞዴል ፈተናዎች ጥገኛ እንደሆኑ ክልላዊ ፈተናው በተማሪዎች እንዲሁም በመምህራን ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ በተጨማሪም የ8ኛ ክልላዊ ፈተና በመምህራን የማስተማር ስነ ዘዴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ይኸውም በክልላዊ ፈተናው ከፍተኛ ሽፋን የሚሰጣቸውን ይዘቶች መሰረት አድርገው የሚያስተምሩ መሆኑ፣ ክልላዊ ፈተናው የማያተኩርባቸው ከመጽሀፉ ያሉ አንዳንድ ይዘቶች ችላ እንደሚሏቸው ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በአጠቃላይ መምህራን በአመዛኑ ፈተና ተኮር የሆኑ ይዘቶች ናቸው ባሏቸው ላይ ትኩረት እንደሚሰጡ ተስተውሏል፡፡ ሌላው የ8ኛ ክልላዊ ፈተና በክፍል ውስጥ ፈተና ዝግጅትና ስልት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ይኸውም መምህራን ክልላዊ ፈተናውን የሚመስሉ ጥያቄችን እንዲፈትኑ አድርጓቸዋል፡፡ ከዚህ በመነሳት መምህራን የክልላዊ ፈተናውን ለመማር ማስተማር ክንውናቸውና ለክፍል ውስጥ ፈተናቸው እነደ ሞዴል ባይጠቀሙና የመማሪያ መጽሃፉን መሰረት አድርገው የክፍል ውስጥ ክዋኔዎችን ቢተገብሩ እንዲሁም የቋንቋ መምህራን ተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎችን ለማሳደግ ትኩረት ቢሰጡና ከዚያም ተማሪዎችን ለክልላዊ ፈተናው ቢያዘጋጁቸው፣ ክልላዊ ፈተናው ሲዘጋጅ ለሁሉም የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች  ተመጣጣኝ ውክልና ቢሰጠው የሚሉ አስተያየቶች ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡*

# የይዘት ማውጫ


**ርዕስ** **ገጽ**

ምስጋና....i
አጠቃሎ ....ii
የይዘት ማውጫ....iii
የሰንጠረዥ ማውጫ ....v
ምዕራፍ አንድ፤መግቢያ....1
1.1 የጥናቱ ዳራ....1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....3
1.3.የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ....3
1.4 የጥናቱ ዓላማ....4
1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ ....4
1.6.የጥናቱ ወሰን ....5
1.7 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ተግባራዊ ብያኔ....5
ምዕራፍ ሁለት ፤ ክለሳ ድርሳናት....6
2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት....6
2.1.1 የፈተና ምንነት ....6
2.1.2.የቋንቋ ፈተና ምንነት....7
2.1.3 የቋንቋ ፈተና አላማ....9
2.1.4 የቋንቋ ፈተና ጠቀሜታ ....10
2.1.5 የፈተና አይነቶች ....11
2.1.6 የፈተና ባህሪያት....13
2.1.7 የወሽባክ ምንነት....15
2.1.8 የወሽባክ አይነቶች....15
2.1.8.1 አዎንታዊ ወሽባክ ....15
2.1.8.2 አሉታዊ ወሽባክ....16
2.1.9 የፈተናዎች ወሽባክ በመምህራን ላይ ያለው ተጽዕኖ....17
2.1.10 በተማሪዎች ላይ የፈተና ወሽባክ ተጽዕኖዎች ....20
2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ....21
ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ....24
3.1 የጥናቱ ንድፍ....24
3.2 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች....24
3.3 የንሞና አመራረጥ ዘዴ ....24
3.3.1 የትምህርት ቤቶች ንሞና አመራረጥ ....24
3.3.2 የመምህራን ናሙና አመራረጥ....25
3.3.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ....25
3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ....26

3.4.1 ሰነድ ፍተሻ ....................26
3.4.3 ቃለ መጠይቅ ....................27
3.4.4. የክፍል ውስጥ ምልከታ ....................27
3.5 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ....................27
ምዕራፍ አራት ፤ የመረጃ ትንተና እና ማብራሪያ ....................28
4.1 የመረጃ ትንተና ....................28
4.2 የውጤት ማብራሪያ ....................53
ምዕራፍ አምስት፤ማጠቃለያ መደምደሚያ እና አስተያየት ....................56
5.1.ማጠቃለያ ....................56
5.2. መደምደሚያ ....................57
5.3 አስተያየት ....................58
ዋቢ መጻህፍት ....................59
አባሪዎች ....................63

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 4.1 የ2011 ዓ.ም እና የ2012 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የማጠናቀቂያ ፈተና የይዘት ስርጭት........................................................................................................29

ሰንጠረዥ 4.2 የማጠናቀቂያ ፈተናው በተማሪዎች መማር ላይ ያለው ተፅዕኖ በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎችና ትንተና ........................................................................................31

ሰንጠረዥ 4.3 ክልላዊ ፈተናው በመምህራን የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴና ትግበራቸው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ትንተና................................................................................37

ሰንጠረዥ 4.4 የክፍል ውስጥ ተግባራትን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች እና ትንተና....41

ሰንጠረዥ4.7 በክፍል ምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ...................48

# ምዕራፍ አንድ፤መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ፈተና የአንድ ትምህርት መማር ማስተማር ሂደት አካል ነው፡፡ ፈተና ተማሪዎች ያስተማርናቸውን ትምህርት ምን ያህል ተረድተውታል የሚለውንና የማስተማር ስልታችን ምን ያህል ውጤታማ ነው የሚለውን ለመመርመር ይረዳል፡፡ ፈተና የተማሪዎችን እድገት በየጊዜው ለመከታተልና ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል የመማር ማስተማር አካል ነው፡፡ ፈተና በመማር ማስተማር ውስጥ ወሳኝ ሚና አለው፡፡ የፈተናን ምንነት በተመለከተ የተለያዩ ሙህራን በተለያየ መንገድ ሲበይኑት የሚታይ ቢሆንም በብያኔዎቻቸው የሚያነሱዋቸው ሃሳቦች ግን ከሞላ ጎደል ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል፡፡ ከነዚህ ሙህራን መካከልም፡- ስዩም ከበደና ሌሎች (1994 ፣68) Richardsen(1989) በመጥቀስ ፈተና ዋና ትኩረቱ በቋንቋ ትምህርት ሂደት የተገኘውን የአሰራር ለውጥና የተካበተውን እውቀት መመዘን ነው፡፡ Bachman (1990፣54) ፈተና በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ የሚያስችልን ጠቃሚ መረጃዎችን የሚሰጥ መሳሪያ ነው፡፡Thorndik (1977) ደግሞ ፈተና በስርዓተ ትምህርቱ የሚመራ እና የትምህርቱን ዓላማዎች ተከታትሎ ተማሪዎች ምን ተምረዋል? ምን አልተማሩም? ምን አውቀዋል? ምን አላወቁም? በማለት የሚጠይቅና ይህንኑ የሚያረጋግጥ የመማር ማስተማር አካል ነው በማለት ገልፆታል፡፡

ወሽባክን የተለያዩ ሙህራን የተለያዩ ብያኔዎች ሰጥተውታል፡፡ Shohamy et al. (1996፣ 288) ወሽባክን ሲገልጹት " በመማር እና በመፈተን መካከል ያለ ግንኙነት ነው፡፡ የፈተናን ተጽዕኖ ( ወሽባክን) በተመለከተ በርካታ ብያኔዎች ቢሰጡም አሁን አሁን ይበልጥ ተቀባይነት እያገኘ የመጣው "ወሽባክ ፈተና በቋንቋ ማስተማርና መማር ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ ነው"(Cheng 2004) እንዲሁም Tayler (2005) ወሽ ባክ ፈተናዎች በትምህርት ሂደቶች ላይ በተለያየ መንገድ ተፅዕኖ ማሳደር እንደሚችሉ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የሚታመን ጉዳይ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ Alderson እና Wall(1993) እንዲሁ ፈተና በመምህራንና በተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ አዎንታዊና አሉታዊ ነገሮች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድር ሀይል እንዳለው ይገልፃሉ፡፡ አገኘሁ (2006) Madus (1988፣ 83)ን ጠቅሰው እንደገለፁት መምህራን ምን ማስተማር እና እንዴት ማስተማር እንዳለባቸው እንዲሁም ተማሪዎች ምን መማር እና እንዴት መማር እንዳለባቸው የመወሰን አቅሙ እየጎለበተ እየመጣ ያለው መደበኛ ስርዓተ ትምህርቱ (Official standard

curriculm) ሳይሆን ፈተና ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ፈተና በክፍል ውስጥ በመምህራንና በተማረዎች የሚከናወኑ ተግባራትን የመወሰን ትልቅ ሚና እየኖረው የመጣ መሆኑ ነው፡፡ በጠቃላይ ፈተና ከመማር ማስተማር ሂደት ጋር የተጣመረ ፤የመማር ማስተማሩ ሂደት አንዱና ዋነኛው አካል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የቋንቋ ፈተና የተማሪውን የቋንቋ ችሎታ የሚለካ ብቻ ተደርጎ መታየት የለበትም፡፡ ምክንያቱም የቋንቋ ፈተና የመምህሩን የማስተማር ተግባር ውጤታማነት የሚለካበት መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡ ስለዚህ በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ መማር አንዱና ዋነኛው ተግባር ቢሆንም መማርን የምንለካበት ፈተና ደግሞ አይቀሬ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡Wantanabe (2006) በተማሪዎች መማር ላይ የሚከሰተው የፈተና ተፅዕኖ በመምህራን በክፍል ውስጥ ከሚተገበሩት ጋር የሚመሳሰልና ወደዚያ የሚሀድ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡ይህን ሀሳብ Cheng (2002) ሲያጠናክሩ ውጫዊ (የማጠናቀቂያ ፈተናዎች) መምህራን ለፈተና እንዲያስተምሩ ማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች ለፈተና እዲማሩ የሚያደርግ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

Hopkins,DK (1998) and Bachman,L.F (1990) እንደተጠቀሰው በአጠቃላይ ፈተና አስራ አምስት ተፅዕኖዎች አሉት፡፡ እነሱም፡- ፈተና በማስተማርና በመማር ፣ መምህራን በሚያስተምሩት ይዘት ፣ መምህራን የማስተማር ስነ-ዘዴ ፣ ተማሪዎች በሚማሩት ጉዳይ እና እንዴት እንደሚማሩ ፣ በማስተማር ፍጥነትና ቅደም ተከተል ፣ በመማር ፍጥነትና ቅደም ተከተል፣ በማስተማር ደረጃና ጥልቀት ፣ በመማር ደረጃ እና ጥልቀት እንዲሁም መምህራን በሚያስተምሩት የትምህርት ይዘትና የማስተማር ዘዴ አመለካከት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ፈተና ጠቃሚ የሆነም ጠቃሚ ያልሆነም ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ ፈተና በሁሉም ተማሪዎችም ሆነ መምህራን ላይ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ ፈተና በጥቂት ተማሪዎችም ሆነ መምህራን ላይ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ከነዚህ ተፅዕኖዎች መካከል ፈተና በመምህራንና በተማሪዎች ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ የፈተሸ ነው፡፡ ስለሆነም የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናው በመምህራንና በተማሪዎች ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ ለመመርመር ተሞክሯል ፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ወሸባክ ፈተናዎች በትምህርት ሂደቶች ላይ በተለያ መንገድ ተፅዕኖ ማሳደር እንደሚችሉ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የሚታመን ጉዳይ መሆኑን (Tayler 2005) ይገልፃሉ፡፡ ሆኖም ግን ፈተና በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ጥናቶች በተለያዩ ውጤቶች ገልፀውታል፡፡ ከእነዚህም መካከል፡- አንጓች (2011) የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተና በጎንደር ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቤቶች በመምህራን የማስተማር ሂደት ላይ ተፅዕኖ እንዳለው ተገልጧል፡፡ የአገኘሁ (2006) ጥናት እንደሚያመለክተው ደግሞ ፈተና በመምህራንና በተማሪዎች ግንዛቤና ተግባር ላይ በአብዛኛው ጠንካራ የሚባል ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑንና ይህም ተፅዕኖ የመማር ማስተማር ሂደቱ ፈተና ተኮር እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በተቃራኒው Alderson እና wall (1993) ጥናት ላይ እንደተገለፀው ፈተና በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተፅዕኖ እንደሌለው ተገልጧል፡፡

ስለሆነም ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በተማሪዎች መማር ላይ ያለው ተፅዕኖ፣ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በመምህራን የመማር ማስተማር ስነ ዘዴና ትግበራቸው ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ፣ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በክፍል ውስጥ ፈተና ዝግጅትና ስልት ላይ ያለው ተፅዕኖ፣ የተከሰቱ የወሸባክ አይነቶች ምን እንደሚመስል ጥናት የሚያስፈልገው በመሆኑ በአጥኝዋ በመታመኑ በመነሻ ሀሳብነት የሚቀርብ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ አጥኚዋ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባስተማረችበት ወቅት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር ያላቸው ፍላጎት አናሳ በመሆኑና ይህም ሊሆን የቻለው በክልል ደረጃ የሚሰጠው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማጠናቀቂያ ፈተና ያመጣው ተጽዕኖ ይሆን? የሚለውን ለመፈተሽ አነሳስቷታል፡፡

በተጨማሪም አጥኚዋ ባለችበት አካባቢ በዚህ የክፍል ደረጃ እና የጥናት ርዕስ ላይ ጥናት ያልተደረገ በመሆኑ ለማጥናት ተነሳስታለች፡፡

## 1.3.የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ጥናቱ በቸሃ ወረዳ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና ተፅዕኖ ምን ይመስላል? የሚለውን የሚመልስ ሲሆን ከዚህ መሪ ጥያቄ በመነሳትም የሚከተሉትን ዝርዝር ጥያቄዎች ይመልሳል ተብሎ ይታመናል፡፡

1.የ2011 ዓ.ም እና የ2012 ዓ.ም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የ8ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና ምን ይመስላል?

2. የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናው በተማሪዎች መማር ላይ ያለው ተጽዕኖ ምን ይመሰላል?

3. የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናው በመምህራን የመማር ማስተማር ስነዘዴና ትግበራቸው ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ምንድን ነው?

4. የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በክፍል ውስጥ ፈተና ዝግጅትና ስልት ላይ ያለው ተጽዕኖ ምንድን ነው?

5. በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ምክንያት የተከሰቱ አወንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች ምንምን ናቸው?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በቸሃ ወረዳ የሚገኙ አራት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተማሪዎችና በመምህራን ላይ ያለዉ ተፅዕኖ መፈተሽ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1.የ2011 ዓ.ም እና የ2012 ዓ.ም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና መፈተሽ፤

2. የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናው በተማሪዎች መማር ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ መተንተን፤

3. የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናው በመምህራን የማስተማር ስነዘዴና ትግበራቸው ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ መመርመር፤

4. የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናው በክፍል ውስጥ ፈተና ዝግጅትና ስልት ላይ ያለውን ተጽዕኖ መመርመር፤

5. የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናው ወሽባክ ምክንያት በቋንቋ ትምህርቱ ላይ የታዩትን አወንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች መፈተሽየሚሉት ናቸው፡፡

## 1.5.የጥናቱ ጠቀሜታ

በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ተፅዕኖ ላይ የተካሄደው ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

- ጥናቱን ትምህርት ቤቶች ዘንድ በማድረስ መምህራን ቋንቋውን ለማስተማር በማጠናቀቂያ ፈተናው ላይ ያላቸውን ጥገኚነት ሊቀንስ ይችላል፡፡

- በየዓመቱ የሚዘጋጁት የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት ለአዘጋጆች እንደ አንድ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡
- የማጠናቀቂያ ፈተናው በቋንቋው ትምህርት ላይ እያሳደረ ያለውን ተፅዕኖ በማሳየት ለትምህርት ባለድርሻ አካላት የቋንቋን ትምህርት አሰጣጥ ለማሻሻል የሚያግዝ መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡
- ወደፊት በዚህ ርዕስ ዙሪያ በስፋት ማጥናት ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች የተወሰነ መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 1.6.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በደቡብ ብሄርብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በጉራጌ ዞን በቸሃ ወረዳ የሚገኙ አራት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች  የተካሄደ ሲሆን የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በተማሪዎችና በመምህራን ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ የፈተሸ ነው፡፡ በደቡብ ክልል ያለፉት ሁለት ተከታታይ አመታት የተዘጋጀውን ፈተና  ማለትም የ2011 ዓ.ም እና የ2012 ዓ.ም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ የ8ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና ተፈትሿል፡ ፡በመሆኑም ጥናቱ ከደቡብ ክልል ውጭ በሌሎች ክልሎች የሚሰጡትን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ ፈተናዎችን ወሽባክ አይመለከትም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጥናቱ በዚሁ ቦታ ተፅዕኖ በተማሪዎችና በመምህራን ላይ የሚያሳድረ ውን ተፅዕኖ ብቻ ይመለከታል፡፡ ከዚህ ውጭ ወሽባክ በሌሎች አካላት ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ አይመለከትም፡:

## 1.7 የቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ተግባራዊ ብያኔ

- የፈተና ተፅዕኖ - ፈተና በመማር መስተማር ላይ የሚያስከትለው ተፅዕኖ
- አወንታዊ ፈተና ተፅዕኖ -ፈተና በመማር ማስተማሩ እንዲኀለብት የሚያስከትለው በጎ ጎን
- አሉታዊ ፈተና ተፅዕኖ- ፈተና በመማር ማስተማሩ ላይ የሚያስከትለው ጎጅ(አሉታዊ) ጎን፤

# ምዕራፍ ሁለት ፤ ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 የፈተና ምንነት

ፈተና በአስተዳደራዊ ትዕዛዝ የሚዘጋጅና የሚተገበር ሲሆን ሊሰጥ የታሰበው ትምህርታዊ ክፍል ተሰጥቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ተማሪዎች የቀሰሙትን እውቀት መጠን ለማረጋገጥ ሲባል በውል የሚታወቅና ስርዓተ ትምህርቱ ባስቀመጠው የጊዜ ክልል ውስጥ የሚፈፀም የማጠቃለያ ተግባር ነው በማለት ( Brown 2002) ይገልጹታል፡፡ Thorndik (1977) ደግሞ ፈተና በስርዓተ ትምህርቱ የሚመራ እና የትምህርቱን ዓላማዎች ተከታትሎ ተማሪዎች ምን ተምረዋል? ምን አልተማሩም? ምን አውቀዋል? ምን አላወቁም? በማለት የሚጠይቅና ይህንኑ የሚያረጋግጥ የመማር ማስተማር አካል ነው በማለት ገልፆታል፡፡

Mehrens (1974 ፣3) ፈተና ተከታታይ ጥያቄዎችን ለመላሾች በማቅረብ መላሾች ለቀረበላቸው ጥያቄዎች ከሚሰጡምላሽና ከሚገኘው ውጤት በመነሳት የመላሾችን ባህሪ መለካት የሚያስችል መሳሪያ ነው በማለት ይበይነዋል፡፡

ፈተና ማለት በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎችን የሚሰጥ መሳሪያ ነው፡፡ ፈተና በስርዓተ ትምህርትና በመርሃ ትምህርት የሚመራና የትምህርቱን ዓላማዎች ተከትሎ ተማሪዎች ምን ተምረዋል? ምን አልተማሩም? ምን አውቀዋል?ምን አላወቁም? በማለት የሚጠይቅና ይህንኑ የሚያረጋግጥ የመማር ማስተማር አካል ነው፡፡ የተለያዩ ባለሙያዎች የፈተና ምንነትን እንዲህ ይገልጹታል፡፡ ያለው (2009፣194) ፈተና ማለት የተወሰኑ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ወጥነት ባለው መንገድ የተፈታኞችን አዕምሯዊ ወይም ስነ ባህሪያዊ ሁኔታ አስመልክቶ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዳ መለኪያ ነው፡፡ ፈተና ማለት ተማሪዎች የተማሩትን ስርዓተ ትምህርትን ምን ያህሉን በሚገባ እንደጨበጡትና ለማረጋገጥ የሚረዱ የልዩልዩ ጥያቄዎች ስብስብ ነው፡፡

Brown (2002፣ 251) ከዕለት ዕለት የመማር ማስተማር ተግባር ጋር የተያያዙ ፣ ዓላማ ያለው እና ተፈላጊውን የተማሪ ችሎታና እውቀት መለካት የሚያስችል ዘዴ ነው በማለት ፈተናን ይገልፁታል፡፡ ፈተና ማለት ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ

እንዲገነዘቡ፣እንዲከታተሉና እነዲያስተውሉ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘቡ ፣ምን ያህል እንዳስተዋሉና እንደተከታተሉ የምንፈትሽበት ፣ትምህርቱ ያስከተለውን የባህሪ ለውጥ የምንመረምርበትና የዳበረውን ብቃት የምንለካበት መሳሪያ ነው ብለዋል፡፡ ፈተና ማለት ተገቢነት ባላቸው ቃላት ተቀነባብሮ በትልም የሚመራ የተማሪዎችን የግል ችሎታና እውቀት በተወሰነ የትምህርት ዘርፍ የምንለካበት መሳሪያ ነው በማለት ብያኔውን ያስቀምጣል ፡፡

Brown(1991፣ 33)እንደገለፁት ፈተና ተፈታኙ የተዘጋጀለትን ትምህርት ምን ያህል መስራት እንደቻለ ወይም እንዳወቀ ለመገንዘብ የሚያግዝ አሰራር (ሂደት) ነው በማለት ይገልፁታል፡፡ ፈተና ለአንድ ትምህርት ፕሮግራም የተቀመጡ አላማ በተማሪዎች ምን ያህል ተፈፃሚ እንደሆነ ወይም ግብ መምታቱንና አለመምታቱን ከሚረጋገጥባቸው መሳሪያዎች አንዱ ነው፡፡ ፈተና ተማሪዎች ምን እንደሚያውቁ ፣የተለያዩ ተግባራት እንዴት እንደተከናወኑ ወይም ምን እንደሚፈልጉ ለማወቅ ሲፈለግ ተገቢ ጥያቄዎች በመጠየቅ በቂ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ መሳሪያ ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ ከተነሳው የሙህራን ብያኔዎች በመነሳት ስለፈተና ምንነት መረዳት የሚቻለው ፈተና ለአንድ የትምህርት ፕሮግራም የተቀመጠን ዓላማ በተማሪዎች ምን ያህል ተፈፃሚ እንደሆነ፣ምን ያህል ዓላማው ከግብ እንደደረሰ የሚያረጋግጥባቸው መሳሪያዎች መሆናቸውን በዋናነት ለመረዳት የሚያስችል ብቃት መሆኑን መገንዘብ የቻላል፡፡ ስለዚህ ፈተና ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት ምን ያህል ተገንዝበውታል የሚለውንና የማስተማር ስልትን ምን ያህል ውጤታማ ነው የሚለውን ለመመርመር የሚረዳ መለኪያ ነው፡፡

## 2.1.2.የቋንቋ ፈተና ምንነት

የቋንቋ ፈተና ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ፈተና ለየት ይላል፡፡ ምክንያቱም የቋንቋ ትምህርት ለማስተማር ካለው ዓላማ የሚነሳ መሆኑ ነው፡፡ የቋንቋ ፈተና አስመልክተው ሙህራን ያስቀመጡተን ብያኔ እንመልከት፡፡

Hughes (2003) የቋንቋ ፈተና ተከታታይ ጥያቄዎችን በማቅረብ ተማሪዎች ያላቸውን የቋንቋ ችሎታ አውጥተው እንዲያሳዩ ለማድረግ የሚያስችል ስልት ነው በማለት ይገልፃሉ ፡፡ የቋንቋ ፈተና ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ላይ የሚያሳዩትን መሻሻል ወይም የቋንቋን

ችሎታ በአጠቃላይ የሚያስመዘግቡትን የባህሪ ለውጥ ለመገምገም ይረዳል በማለት ያብራራሉ፡፡

የቋንቋ ፈተና ከቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ጋር የተጣመረ የቋንቋ መማር ማስተማሩ ሂደት አንዱና ዋነኛው አካል ነው፡፡በመሆኑም የቋንቋ ፈተና፣ በቋንቋ መርሀ-ትምህርት ና በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ተመስርቶ የተማሪዎቹን የቋንቋ ብቃት ለመመዘንና ለመለካት በሚል ተግባር ላይ ይውላል በማለት ሙህሩ ይገልፃሉ፡:

Bachman (1990፣ 45) and Huches (2003፣ 6) ስለቋንቋ ፈተና ሲገልፁ ተማሪዎች እያሳዩ ያሉትን የቋንቋ ችሎታን ለማሻሻል መገምገም፣በየትኛው የቋንቋ ችሎታ ወይም ክህሎት ላይ ድክመት እንዳለባቸው የማሳየት፣ በየትኛው የትምህርት ክፍል ማስተካከል እንደሚሻው መጠቆም ፣ተማሪዎች የበለጠ እንዲሰሩና እንዲነቃቁ ፣የመምህራን የትምህርት አቀራረብ ውጤታማነት ከተማሪዎች ውጤት አንፃር የመመርመር ዓላማዎች እንዳላቸው በጽሁፋቸው ገልፀዋል፡፡

Alderson, Clap ham እና wall (2001፣ 6) በበኩላቸው ደግሞ በቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ፈተና ስንል በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ላይ ልዩልዩ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ የሚረዱና ከተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ማግኘት የሚያስችል ዘዴ በመሆኑ ፈተና የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ፣ ድክመትና ጥንካሬ ወ ዘ ተ መመርመር ማወቅ የሚያስችል መሳሪያ ነው በማለት የቋንቋ ፈተናን ይገልፁታል፡፡

ከዚህ በላይ የቀረበዉን የሙህራን ሀሳብ ጠቅለል አድርገን ስንመለከት የቋንቋ ፈተና ከቋንቋ ትምህርት ጋር ጥብቅ የሆነ ቁርኝት ያለዉ ፣የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ፣ እድገት ወይም መሻሻል በተመለከተ መረጃዎችን የሚሰጥ፣ ተማሪዎች ያላቸዉን የቋንቋ ችሎታ ምንያህል አዉጥተዉ ለተግባቦት ስራ ያዉሉታል፣ የቋንቋ ትምህርት አሰጣጡን ጠንካራና ደካማ ጎኑን ለመመዘንና ለመገምገም የሚረዳ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ መዳበሩንና በቋንቋ ችሎታ ተማሪዎቹ የተወዳዳሪነት ስሜት ከማጎልበቱም በላይ ትምህርቱን ምን ያህል ተነቃቅተው እንደተከታተሉ ትልቅ እገዛ የሚያደርግ መሳሪያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

### 2.1.3 የቋንቋ ፈተና አላማ

ፈተና የአንድ ትምህርት መማር ማስተማር ሂደት አካል ነው፡፡ ፈተና ተማሪዎች ያስተማርናቸውን ትምህርት ምን ያህል ተረድተውታል የሚለውንና የማስተማር ስልታችን ምን ያህል ውጤታማ ነው የሚለውን ለመመርመር ይረዳል፡፡ ፈተና በአጠቃላይ በማስተማር ስነ-ዘዴ ስር የሚጠቃለል የመማር ማስተማር ሂደት አንዱ አካል ነው ፡፡ ፈተና ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ እንዲገነዘቡ፣እንዲያስተውሉና እንዲከታተሉ የቀረበላቸውን ትምህርት ምን ያህል እንደተገነዘቡ ፣ ምን ያህል እንዳስተዋሉና እንደተከታተሉ የምንፈትሽበት ፣ትምህርቱ ያስከተለውን የባህሪ ለውጥ የምንመረምርበትና የዳበረውን ብቃት የምንለካበት መሳሪያ ነው፡፡ በተጨማሪም ፈተና የተማሪዎችን ብቃት በሚመለከት ለመመስከር እንደ መነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ብዙ ሰዎች ፈተና ሲባል የሚያስታውሱት ነገር የጽሁፍ ፈተና ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ፈተና በጽሁፍ ፣ በቃል ወይም በተግባር ሊቀርብ እንደሚችል ከየራሳችን ተሞክሮ መገንዘብ እንችላለን፡፡

የቋንቋ ፈተናም ከቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት ጋር የተጣመሩ የቋንቋ መማር ማስተማሩ ሂደት አንዱና ዋነኛው አካል ነው፡፡ በመሆኑም የቋንቋ ፈተና በቋንቋ መርሃ ትምህርቱና በመማሪያ መጽሀፉ ላይ ተመስርቶ የተማሪዎቹን የቋንቋ ብቃት ለመመዘንና ለመለካት በሚል ተግባር ላይ ይውላል፡፡ የቋንቋ ፈተና የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ፣ የሰዋሰውና የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ ለመመዘን የሚያስችል ስልት ነው፡፡ በተጨማሪም የቋንቋ ክሂሎችን ማለትም ማዳመጥ ፣መናገር ፣ማንበብና መፃፍን ለመመዘን ፈተና ጠቃሚ ነው ፡፡

የቋንቋ ፈተና የራሱ የሆነ አላማ ሊኖረው እንደሚገባ ይታወቃል፡፡ ከዚህ የተነሳ ማንኛውም የቋንቋ ፈተና አላማ ከሌለው ውጤታማ አይሆንም፡፡ ከበርካታ የቋንቋ ፈተና አላማዎች ውስጥ ፈተና በአንድ የትምህርት ሂደት ውስጥ የታቀዱ ግቦች መሳካታቸውን ለማወቅ የሚያስችል መሳሪያ ነው (Bachman, L, F, & Palmer, A.1996)፡፡

የቋንቋ ፈተና እንደተወሰነለት አላማ ትምህርት ለመጀመር ፣ስራ ለመቀጠር ፣ከቦታቦታ ለመንቀሳቀስ ፣ተማሪዎችን በልዩ ልዩ የትምህርት መስኮች ለመመደብ እንዲሁም የማስተማር ስነ-ዘዴውን ለመገምገም እና አንዳንድ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ የሚያስችል መሆኑን ሙህራን ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም በጥሩ ሁኔታ የተደራጀ ፈተና ስለተፈታኞች

ችሎታ ጥሩ መረጃ የሚሰጥ ነው፡፡ በተጨማሪም የአንድ ፈተና ዋና አላማ ለፈተናው ከሚሰጠው ምላሽ በመነሳት ተፈታኞችን መመዘን ነው (Weir C.J 1990)::

### 2.1.4 የቋንቋ ፈተና ጠቀሜታ

የቋንቋ ፈተናን ጠቀሜታ ፈተናውን ለመስጠት ያነሳሳን አላማ ይወስነዋል፡፡ እንደ ሙሁራኑ ገለፃ ፈተና ማስተማርን መከተል ብቻ ሳይሆን ለቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ድጋፍ ሊሰጥ የሚችል መሆን አለበት፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት ዋነኛው የትኩረት ነጥብ ተማሪው ነው፡፡ ትኩረቱም በሚከተለው የቋንቋ ትምህርት ተገቢውን እድገትና መሻሻል እንዲያሳይ ማድረጉ ላይ ሲሆን ይህንን ሁኔታ ወደ ተግባር ለማሻገር ደግሞ የተማሪው ችሎታ በየጊዜው መመዘን ሲኖርበት ዋናው መሳሪያ ፈተና ይሆናል በማለት ያብራራሉ፡፡ ዘርዘር ባለ መልኩ ሲገልፁት የቋንቋ ፈተናዎች የተማሪዎችን መሻሻል ለማወቅ፣ድክመትና ጥንካሬያቸውን ለመመርመር፣የወደፊቱን የትምህርት አሰጣጥ ለማስተካከል፣ተማሪዎች የበለጠ እንዲሰሩ ለማበረታታት ፣ለማነቃቃት ጠቀሜታቸው የላቀ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በአጠቃላይ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የቋንቋ ፈተናዎች የትምህርቱ አካል ሆነው የትምህርቱን አሰጣጥ በማጠናከር የትምህርት አላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ በማድረግ በኩል የላቀ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ይህንኑ ጠቀሜታ ማበርከት የሚችሉት ግን በተገቢው መንገድ ሳይንሳዊ መርህን ተከትለው መዘጋጀት ሲችሉ ብቻ እንደሆነ የሙህራኑ ሀሳብ ያስገነዝባል፡፡

ቀደም ባሉት ዘመናት ቋንቋ ማሰተማር እና ቋንቋን መፈተን ግንኙነት እንደሌላቸውና ፈተናዎች በመማር ማስተማር ሂደት ሚና አልባ ተግባሮች እንደሆኑ ይታመን ነበር (Harrison.1989):: ነገር ግን ቋንቋን ማስተማርና ቋንቋን መፈተን እርስ በእርስ የተቆራኙ እና የማይለያዩ ተግባሮች እንደሆኑ ሌሎች ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ፈተና የተማሪዎችን እድገት በየጊዜው ለመከታተልና ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል የመማር ማስተማር አካል ነው ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም ፈተና ተማሪዎችን ለማበረታታት እድገትና መሻሻላቸውን ለመከታተል የመማር ችግሮችን ለይቶ የመፍትሄ ሀሳብ ለመስጠት ፣ ስርዓተ-ትምህርቱን ለማሻሻልና በአጠቃላይ የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳካ እንዲሆን ለማድረግ አላማ ይዞ ከመካሄዱ አንፃር ከማስተማር ተግባር ተለይቶ እንደማይታይ ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ የቋንቋ ትምህርትና ፈተና የማይነጣጠሉ ተግባሮች ናቸው፡፡ ከቋንቋ

ፈተና ውጭ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ አላማ በትክክል እየተጓዙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያዳግታል፡፡ የተማሪዎችን ማንነት ፣ የቋንቋ ችሎታ፣ድክመትና ጥንካሬ በማወቅ በኩል መምህራንን የሚያስተካክል ባለመኖሩ ከማንኛውም ፈተና ይልቅ መምህሩ የሚያዘጋጃቸው የበለጠ ቦታ ይይዛል፡፡ በአጠቃላይ ቋንቋን ማስተማርም ሆነ መፈተን የማይነጣጠሉ ከመሆናቸው አንጻር ሁለቱም በተገቢው መንገድ ሊከናወኑ ይገባል፡፡ በወጉ የተዘጋጀ ፈተና በመማር ማስተማሩ ሂደት አወንታዊ ሚና ሲኖረው ይህ ካልሆነ ግን ውጤቱ የተዛባ ስለሚሆን በርካታ ችግሮችን ያስከትላል፡፡

## 2.1.5 የፈተና አይነቶች

የቋንቋ ፈተና አይነቶችን ስንመለከት የተለያየ ይዘት ያላቸው መሆኑን ማለትም የሚመዝኑት ነገር አንድ አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም በማስመልከት Brown(2004 ፣43-47) የፈተና አይነቶችን ከነማብራሪያቸው እንደሚከተለው ያስቀምጣሉ፡፡

## 2.1.5.1. የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና

ይህ ፈተና ከፈተና አይነቶች አንዱ ነው፡፡ ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ የተለመደ አይደለም፡ ፡ምክንያቱም የተማሪዎችን የቅድመ ችሎታ ለመለካት የሚውል ሲሆን ይህንን የቅድመ እውቀት ለመመዘን የተመደበ በመሆኑ ነው፡፡ የቅድመ ችሎታ መለኪያ የሚዘጋጀው የተማሪዎችን የቅድመ እውቀት ለመለካትና በአንድ ተግባር ላይ ምን ያህል ብቁ እንደሆኑ ለማወቅ ነው፡፡ በአጠቃላይ የዚህ ፈተና ዓይነት መለካት የሚቻለው ተማሪዎች በምንም አይነት ስልጠና ሳይታገዙ የነበራቸውን እውቀት ወይም ችሎታ ለመለካት አገልግሎት ላይ የሚውል መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.1.5.2.የብቃት መለኪያ ፈተና

ይህ የፈተና አይነት ተማሪዎች ሁሉን አቀፍ የሆነ ብቃታቸውን ለመለካት የሚያስችል ነው፡፡የብቃት መለኪያ ፈተና በአንድ በተወሰነ ኮርስ ወይም አንድን ነጠላ ክሂል ለመለካት ብቻ የምንጠቀምበት አይደለም፡፡ ይልቁንም አጠቃላይ ብቃታቸውን ለመመዘን የምንጠቀምበት የፈተና አይነት ነው፡፡ በዚህ የፈተና አይነት ደረጃውን የጠበቀ የምርጫ ጥያቄ እና የቃላትን ፣የመመዘን ተግባር አለው፡፡ በአጠቃላይ ይህ የብቃት መለኪያ ፈተና ብዙውን ጊዜ የሚጠቀመው ማጠቃለያ ምዘና (summative) እና እርስ በርስ አወዳድሮ

(norm referenced) የሆኑ የውጤት አያያዞች ነው፡፡ ስለዚህ የብቃት መለኪያ ፈተና ተማሪዎች ያላቸውን አጠቃላይ እውቀት ወይም ብቃት የምንለካበት እና የምንፈትሽበት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 2.1.5.3. ለምደባ አገልግሎት የሚዘጋጅ ፈተና

ለምደባ አገልግሎት የሚዘጋጅ የፈተና አይነት አንዳንድ ጊዜ የብቃት መለኪያ ፈተናን ሚና ሊጫወት ይችላል፡፡ ይህ የፈተና አይነት ዋና ዓላማው የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ወይም ያሉበትን የእውቀት ደረጃ ለመለየት የሚያስችል ነው፡፡ ለምደባ አገልግሎት የሚዘጋጅ ፈተና ብዙውን ጊዜ የማስተማር ተግባሩ ባይጠናቀቅም እንኳን የተማሪዎችን አቅም ወይም ችሎታ ለማወቅ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል፡፡ በአጠቃላይ ለምደባ አገልግሎት የሚውል ፈተና ተማሪዎች ያላቸው እውቀት ምን ያህል እንደሆነ ለመመዘን ወይም ለመለካት የሚያገለግል የፈተና አይነት እንደሆነ መረዳት ተገቢ መሆኑን አይተናል፡፡

### 2.1.5.4.የተማሪዎችን ድክመት ፈልጎ ለማግኘት የሚሰጥ ፈተና

ብዙውን ጊዜ ለምደባ አገልግሎት የሚውል የፈተና አይነትና ድክመትን ፈልጎ ለማግኘት የሚሰጥ ፈተና ጥልቅ የሆነ ተመሳስሎሽ ይታይባቸዋል፡፡ ድክመትን የሚለይ የፈተና አይነት ተማሪዎች ቋንቋን በመማር ሂደት የሚታይባቸውን ድክመት ለመፈተሽ የሚያስችል የፈተና አይነት ነው፡፡ መምህራን በዚህ ፈተና የተማሪዎችን የመፃፍ ፣የማንበብ ፣ማዳመጥ እና በመሳሰሉት ክሂሎች የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመፈተሽና መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል የፈተና አይነት ነው፡፡

የተማሪዎችን ድክመት ፈልጎ የማግኘት ፈተና እና የብቃት መለኪያ ፈተና ተመጋጋቢነት የሚያሳዩበት ዋና ጉዳይ የብቃት መለኪያ ፈተና የተማሪውን እውቀት የሚለካ ሲሆን ድክመትን ፈልጎ ማግኛ ፈተና ደግሞ በብቃት መለኪያ ፈተና ጊዜ የታየውን ክፍተት ወይም ችግር ፈልጎ ማገረኘት ነው፡፡ በመሆኑም እርስ በርሳቸው ተመጋጋቢነት ይታይባቸዋል፡፡ ስለዚህ ከዚህ የፈተና አይነት የምንረዳው ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ወቅት የሚታይባቸው የእውቀት ክፍተት ምን እንደሆነ ማሳየት ዋና ተግባሩ እንደሆነ ነው፡፡

## 2.1.5.5.የችሎታ መለኪያ ፈተና

የችሎታ መለኪያ ፈተና ከክፍል ተግባራት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያለው ነው፡፡ ይህም ሲባል ከሚዘጋጀው መርሀ ትምህርትና ከትምህርቱ ምዕራፎች ጋር ቁርኝት ያለውና ለትምህርት አገልግሎት የሚውሉ ግብአቶችን መሰረት ያደረገ፣ውስን ጊዜ ተመድቦለት በትምህርቱ ማብቂያ ላይ የትምህርቱን ዓላማ መሰረት አድርጎ የሚሰጥ የፈተና አይነት ነው፡፡ የችሎታ መለኪያ ፈተና የድክመት መለኪያ ፈተናን ሚና ይጫወታል፡፡ ማለትም ተማሪዎች ያመጡትን ውጤት በመመልከት ወደ ፊት በየትኛው ተግባር ላይ መቀጠል እንዳለባቸውና የትኛውን ክሂል ማሻሻል እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው፡፡ ስለዚህ ይህ የፈተና አይነት ለመማር ማስተማር ሂደት የሚውሉ ግብአቶችን መሰረት በማድረግ የሚሰጥን የትምህርት ዓላማ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተማሪዎች ወደ ፊት የትኛውን ይዘት መማር እነዳለባቸው የሚያሳይ የፈተና አይነት መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

Brown(2004) ከላይ የተጠቀሱትን የፈተና አይነቶች ያስቀመጠ ቢሆንም ተስፋዬ (1981)ደግሞ የፈተና አይነቶችን በአራት ይከፍሏቸዋል፡፡ እነዚህም የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ፣የደረጃ መለኪያ ፈተና ፣የጥንካሬና ድክመት መለኪያ ፈተና እና የችሎታ መለኪያ በማለት ያስቀምጣሉ፡፡ ይሁን እንጅ የብቃት መለኪያ ፈተናን ከቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና ጋር በማቀናጀት የቀረበ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የቅድስተ ማርያም ሞጁል 1(1995) የፈተና አይነቶችን የቅድመ ችሎታ መለኪያ ፈተና፣ የደረጃ መለኪያ ፈተና እና የጥንካሬና የድክመት መለኪያ ፈተና በማለት ከፋፍሎ ያስቀምጣቸዋል፡፡ ይህንን አከፋፈል ስንመለከተው የችሎታ መለኪያ ፈተናን ከደረጃ መለኪያ ጋር ተመሳስሎሽ አለው በማለት አጣምሮ ያስቀምጠዋል፡፡ በአጠቃላይ የፈተና አከፋፈልን ስንመለከት ሙህራን የሚሰጡት አከፋፈል የተለያየ ቢሆንም የተነሱት ነጥቦች ግን አንዱ ባንዱ ውስጥ ተካተው እንደሚገኙ የሚያነሱትም ጭብጥ ተመሳሳይ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 2.1.6 የፈተና ባህሪያት

ፈተናዎች የሚዘጋጁት የተማሪዎችን የቋንቋ ክህሎትና እውቀት ለመለካት ከመሆኑ አንፃር መምህራን ይህንኑ አላማ ማሳካት ይችሉ ዘንድ የሚያዘጋጇቸው ፈተናዎች ጥራት ያላቸው እንዲሆኑ መጨነቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ከሆነ ፈተናው የሚሰጠው መረጃ ትክክለኛ

ስለሚሆን ከመረጃው በመነሳት የሚሰሩ ቀጣይ ስራዎች ውጤታማ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የቋንቋ ፈተና የተለያዩ ባህሪያት አሉት፡፡ እነዚህ ባህሪየት የሚከተሉት ናቸው፡፡

## ሀ.ፅኑነት

ፈተናው የተሳለበትን ተግባር ማሳካቱንና የታለመለትን ግብ ማሳካቱን ማሳያመንገድ ነው፡፡ (call han እና clark 1988. 34-60) በተመሳሳይ መንገድ (Brown 2007,19) ፅኑነትን በአንድ ፈተና አስቀድሞ ቢዘጋጅ ምን እንዲለካ ታሰበ በተጨባጭስ ምን ለካ ፈተናው ያሰበለትን መረጃ ማስገኘት ችሏል ወይስ አልቻለም የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ የሚያስችል ነው በማለት ይገልፁታል፡፡ ፅኑነት የአንድን ፈተና አላማ ማሳካት አለማሳካቱን የሚያመለክትና ፈተናው መለካት የተፈለጉ ችሎታዎችን እንደየ ደረጃቸው ትኩረት ሰጥቶ በትክክል መለካቱን መቆጣጠሪያ ስልት ነው ይሉታል፡፡ በአጠቃላይ አንድ ፈተና እንዲለካ የታሰበውን ክህሎት ወይም እውቀት መለካት ከቻለ ጽንኡ ነው ይባላል፡፡

## ለ.አስተማማኝነት

Alderson, Clapham እና Wall (2001:87) እንዲሁም Hughes (1989;29) እና ሌሎችም እንደሚገልፁት አስተማማኝነት አንድ ፈተና ወይም ሁለት ተመጣጣኝ ፈተናዎች ወይም የአንድ ፈተና ሁለት ክፍሎች ለተመሳሳይ ተማሪዎች ከአንድ ጊዜ በላይ ተሰጥተው የሚገኘውን ውጤት ወጥነት (ተመሳሳይነት) የሚያመለክት መሆኑን ይስማሙበታል፡፡ አስተማማኝነት ያለው ፈተና በውስጡ የያዛቸው ጥያቄዎች እርስ በርስ የተዛመዱና አንድን ባህሪ ወጥ በሆነ መልኩ ለመለካት የሚችሉ ይሆናሉ፡፡

## መ.ተተግባሪነት

Brown (1980 ፣ 253) አንድ ፈተና ተተግባሪ መሆን አለበት ሲባል በገንዘብ አቅም ፣ጊዜና የሰው ሀይል፣ፈተናውን ከመፈተንና ውጤቱን አርሞ ከመተርጎም አንፃር ያለውን የተፈፃሚነት ሁኔታ ይመለከታል ሲሉ ገልፀዋል፡፡ Weir(1993;21) በበኩላቸው ተተግባሪነት ከጊዜ ፣ጉልበትና ከማቴሪያል አቅም ጋር ተያይዞ የሚታይ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

## ሠ.ትክክለኛነት

ለምዘና ወይም ለፈተና የሚመረጡ ተግባራት አውዳዊ የሆኑ ፣እውነተኛ የሆኑ እና በይዘታቸው የሚያሰለቹ ሳይሆኑ የተማሪዎችን ስሜት የሚስቡ መሆን አለባቸው፡፡

### 2.1.7 የወሽባክ ምንነት

ወሽባክ ተማሪውን የቋንቋ ፈተና ፈትነን በመጨረሻ ላይ ውጤቱ በተማሪው ላይ የሚፈጥረው ተጽዕኖ ነው፡፡ ወሽባክ በተግባራዊ ስነ-ልሳን አንድ የጥናት መስክ ሲሆን ፈተናዎች ቋንቋ ማስተማርና መማር ላይ የሚፈጥሩት ተፅዕኖ ነው፡፡ ታሪካዊ ዳራው እንደሚያሳየውም ፈተና ማስተማር መማር ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ ከአጠቃላይ ትምህርትና በተግባራዊ ስነ-ልሳን ጽሁፎች ከፍተኛ ቦታ እያገኘ የመጣው ከ1990ዎቹ ወዲህ ቢሆንም በተለይ በአጠቃላይ የትምህርት መስክ ግን ከተጠቀሰው ጊዜ ቀደም ያለ የፈተና ጥናት አንድ ገፅታ ነው፡፡ ይህም ጉዳይ በአጠቃላይ ትምህርት መስክ አብዛኛውን ጊዜ ባክዋሽ በመባል የሚታወቅ ሲሆን በተግባራዊ ስነ-ልሳን ወሽባክ በሚል ስያሜ ይጠራል አገኘሁ(2006)፡፡

### 2.1.8 የወሽባክ አይነቶች

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የፈተና ወሽባክ በሁለት አበይት ጉዳዮች ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነሱም በትምህርት ሂደቱ ላይ በሚያደርሰው ጠቃሚና ጎጅ ተጽዕኖ መሰረት አዎንታዊ እና አሉታዊ ወሽባክ በማለት ይከፈላል፡፡

#### 2.1.8.1 አዎንታዊ ወሽባክ

Cheng እና Curtis (2004) ፣የ Pearson (1988) ጥናት በመጥቀስ እንደገለጹት የፈተናዎች ተጽዕኖ ጠቃሚ ሆኖ ሲገኝ እና ተፈላጊ ለውጦች እንዲመጡ የሚያበረታታ ሲሆን የወሽባክ አይነቱ አዎንታዊ ነው ይባላል፡፡ ስለሆነም አዎንታዊ ወሽባክ ፈተናው ጥሩ የመማር ማስተማርን ክንውን የሚያበረታታ ሲሆን የሚፈጠር ነው፡፡ Hughes (1989) አዎንታዊ ወሽባክን የሚገልጹት "የንግግር ችሎታን ለማሳደግ ከፈለግህ የንግግር ችሎታን ፈትን "(if you want to encourage oral ability ,then test oral ability) በማለት ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው አዎንታዊ የፈተና ወሽባክ እንዲከሰት ቀጥታ መፈተን አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡

Alderson እና Wall (1993) እንደሚገልጹት አዎንታዊ ወሸባክ መምህራንና ተማሪዎች የመማርና የማስተማር ግቡን ለማሳካት ተነሳሽ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም አዎንታዊ ወሸባክ የሚባለው የመፈተኑ ሂደት (ቅደም ተከተል) ውጤት ጥሩ የማስተማር ተግባራትን ሲያበረታታ ነው በማለት (Hughes፣1989 እና 2003 ፣ Bailey ፣1999) ይገልጻሉ፡፡ ስለሆነም አዎንታዊ ወሸባክ የመማር ማስተማሩ ክንውን የተቃና እና የተሳካ እንዲሆን ያስችላል ማለት ነው፡፡ ይህን ሃሳብ Pearson(1988) ሲያጠናክሩ ጥሩ ፈተናዎች በመማር ማስተማር ተግባራት ላይ ከዋሉ አዎንታዊ መማር ማስተማር ሂደትን ያበረታታሉ በማለት ነው፡፡ Pan (2009) ደግሞ አዎንታዊ ወሸባክን እንደሚከተለው አሳጥረው አቅርበውታል፡፡

- መምህራንንና ተማሪዎችን የመማር ማስተማር ግቦችን ለማሳካት የሚያነሳሳ ከሆነ
- አዎንታዊ ወሸባክ የሚከሰተው ፈተናው መምህራን ትምህርቱን በተሰጠው ጊዜ እንዲሸፍኑ የሚያስችልና መርሀ-ትምህርቱን በተሰጠው ጊዜ እንዲያጠናቅቁ ሲያደርግ ነው ፡፡
- ፈተናው የመማር ማስተማሩን ግብ የሚያሳካ ከሆነ
- ፈተናው ተማሪዎችን ለውጤታማነት ጠንክረው እንዲሰሩ የሚያነሳሳ እና መማርን የሚያበረታታ ከሆነ የፈተናው ወሸባክ አዎንታዊ ነው፡፡

### 2.1.8.2 አሉታዊ ወሸባክ

አሉታዊ ወሸባክ የሚከሰተው ፈተናው ሊዳስስ የሚገባውን ብቃት እና ክህሎት ሳይፈትሽ ሲቀር ነው፡፡ ተገቢውን የፈተና ይዘት አለማካተት እና ትክክለኛውን የፈተና ስልት አለመጠቀም አሉታዊ ወሸባክ በቀላሉ እንዲከሰት ያደርጋል፡፡ Hughes (1989) እንደገለጹት ወሸባክ አሉታዊ የሚሆነው በትምህርቱ ይዘት እና በፈተናው መካከል ተቃርኖ ሲኖር ነው፡፡ Shohamy (1992) ደግሞ አሉታዊ ወሸባክን ሲገልጹት ፈተናው የስርዓተ ትምህርቱን ይዘት ወደ ጠባብነት ሊመራው ይችላል ፣ ተማሪዎች ቋንቋውን የሚማሩት ለቋንቋው ፈተና ነው፡፡ Vernon (1956) ሲገልጹ መምህራን ፈተናውን ከማለፍ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸውን የትምህርት ይዘት እና ተግባራትን ችላ እንዲሏቸው ያደርጋል፡፡ Cheng እና Curits (2004) እነደገለጹት የአጠቃላይ የትምህርት መስክ ሆኑ የቋንቋ ፈተናዎች ብዙውን ጊዜ በማስተማር ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ አሉታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህም ሌላ Cheng እና Curits (2004) እንደሚሉት ፈተናዎች መምህራን ስርዓተ ትምህርቱን አዛብተው እንዲያቀርቡት የሚያደርጉ ከሆነ የፈተናዎች ተጽዕኖ

አሉታዊ ነው ማለት ነው፡፡ እንደ Alderson እና Wall (1993) ደግሞ አሉታዊ ወሽባክ በፈተና ምክንያት በመማር ማስተማር ላይ የሚከሰት የማይፈለግ ተጽዕኖ ነው፡፡ Bachman እና Palmer (1996) ደግሞ ሁለቱም አዎንታዊ እና አሉታዊ ወሽባክ በጠባቡ (Micro-level) በክፍል ውስጥ መቼት እና በሰፊው (Macro-level) በማህበራዊ እና ትምህርታዊ ስልቶች ይከሰታሉ፡፡ ስለሆነም የአሉታዊ ወሽባክ መፈጠር መንስኤዎች እና ውጤቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

- ፈተናዎች የመማር ማስተማሩን ክንውን የበላይነት ሲይዙ (ሲቆጣጠሩ)፣
- በፈተናው አላማ እና በስርዓተ ትምህርቱ አላማ መካከል ያለው ግንኙነት ሲጠፋ ፣
- የትምህርቱ ይዘት እና ለፈተናው ትኩረት የተሰጠበት ይዘት የተለያየ ሲሆን ማለትም ማስተማር እና መፈተን ግንኙነት የማይኖራቸው ከሆነ ፣
- መምህራን ከፈተናው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸውን ይዘቶች እና ተግባራት ለማለፍ ሲሞክሩ፣
- መምህራን ይዘቶችን እና ተግባራትን ከፈተናው ጋር ባልተዛመደ መልኩ መተግበር ሲሞክሩ ፣
- ተማሪዎች እውነተኛውን የቋንቋ ገፅታ ከመማር ይልቅ እንፈተነዋለን ብለው ከሚያስቡት ተናጠላዊ እውቀት ላይ ካተኮሩ የፈተናው ተፅዕኖ አሉታዊ ነው፡፡

## 2.1.9 የፈተናዎች ወሽባክ በመምህራን ላይ ያለው ተጽዕኖ

የማጠናቀቂያ ፈተናዎች በመምህራን የማስተማር ክንውን ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል Yasin(2014) እንደገለጹት ፈተናዎች በተለይም ከፍተኛ ውሳኔ የሚወሰንባቸው መምህሩ በክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚያስተምር ፣ምን እንደሚያስተምር ፣የአጋዥ መጽሃፍ መረጣ ላይ እና የክፍል ውስጥ ፈተና ቅርጽና የአፈታተን ስልት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አላቸው፡፡ Jilani ፣(2009) Alderson እና Wall (1993) ፈተና በመምህሩ ማስተማር ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል፤ ፈተና መምህሩ እንዴት እንደሚያስተምር ተጽዕኖ ሊያደርስ ይችላል፤ ፈተና በማስማሩ ደረጃ እና ቅደም ተከተል ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል፤ ፈተና በማስተማሩ መጠንና ጥልቀት ሊኖረው ይችላል፤ ፈተና ይዘቱን በመማር እና ማስተማር ዘዴ ላይ በሚኖረው አመለካከት ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል ብለዋል፡፡

## ሀ.የፈተናዎች ወሽባክ በመምህራን የማስተማሪያ ስነ ዘዴዎች ላይ ያለው ተጽዕኖ

መምህራን ለተማሪዎቻቸው እውቀታቸውን ለማስተላለፍ የማስተማር ሰነ ዘዴ ወሳኝ ነው፡፡ Borich(1996) የተለያዩ የማስተማር ስነ ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ፡- መምህር መራሽ ፣ሙከራዊ፣ውይይት ፣መጠይቅ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ከነዚህ የማስተማር ስልቶች መምህር ተኮር የማስተማር ስነ ዘዴ በሀገራችን በስፋት የሚስተዋል ነው፡፡ ይህ የማስተማር ስነ ዘዴ በጣም ጥንታዊ እና የሚከተሉት ድክመቶች እንዳሉት Borich(1996) ይገልጻሉ፡፡ድክመቶችም ፡-

- ✓ የተማሪዎችን ግብረ መልስ ይቀንሳል፡፡
- ✓ የተማሪዎችን የመረዳት ደረጃ ትክክለኛ ባልሆነ መልኩ እንዲያስቡ ያደርጋል፡፡
- ✓ ተማሪዎች መረጃዎችን በቶሎ ስለሚረሱ ከትምህርቱ ሂደት ያስወጣቸዋል የሚሉት ናቸው፡፡

Alderson(1993) እና Cheng (1997) በጥናታቸው ምንም እንኳን የትምህርቱ ይዘት በፈተናው ወሽባክ ምክንያት ቢቀየርም የማስተማሩ ስነ ዘዴ እንዳልተቀየረ ገልጸዋል፡፡ Simachew (2012) እንደገለጹት በወሽባክ የተለያየ መንገድ የመምህራን የማስተማር ትግበራ በዋናነት የመምህራን የማስተማር አመለካከት ተጽዕኖ ይደርስበታል፡፡

ከፍተኛ ዉሳኔ የሚወሰንባቸዉ (ብሔራዊ ፈተናዎች) በመምህራን የማስተማር ስነ-ዘዴ እና በክፍል ፈተናቸዉ ላይ ተፅዕኖ ያሳርፋሉ (Luxia፣2005)፡፡ እንዲሁም በእነ Cheng (2002)፣ Spart (2005)፣ Wall እና Alderson (1996) ጥናቶች እንደተጠቀሰዉ ብሄራዊ ፈተናዎች በመምህራን የክፍል ትምህርት ሂደት እና ትግበራ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡

## ለ.ወሽባክ በክፍል ፈተናዎች ላይ ያለው ተጽዕኖ

በክፍል ውስጥ እንደሚከናወነው የማስተማር ስነ ዘዴ ሁሉ በክፍል ውስጥ የሚሰጡ ፈተናዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው ወሽባክ ተጽዕኖ የሚደርስባቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም ከፍተኛ ውሳኔ የሚወሰንባቸው ፈተናዎች መምህራን በክፍል ውስጥ በሚያዘጋጁቸው ፈተናዎች ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በCheng (2002) እንዲሁም Wall እና Alderson (1996) ስራዎች እንደተገለጸው ብሄራዊ ፈተናዎች

በመምህራን የክፍል ምዘና ሂደት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡ የክፍል ውስጥ ፈተናዎች በውጫዊ ፈተናዎች በአዎንታዊ ወይም በአሉታዊ መልኩ ተጽዕኖ ሊደርስባቸው ይችላሉ (Alderson እና Wall ፣1993፣ Shih፣ 2009)::

## ሐ. የትምህርቱን ይዘት በማስተማር እና መርጃ መሳርያ መረጣ ላይ ያለዉ ተፅዕኖ

ወሽባክ መምህራን በማስተማር ክንዉን ወቅት በሚመርጧቸዉ ይዘቶች እና መርጃ መሳርያዎች ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ እንደ Simachew (2012) ገለፃ በወሽባክ የተለያዩ ሁኔታዎች የመምህራን ማስተማር ትግበራ፣ በማስተማር ላይ ያላቸዉ አመለካከት በመጀመሪያ ላይ ተፅዕኖ ይደርስበታል፡፡ እንዲሁም Spart (2005) እና Shih (2009) በወሽባክ ተፅዕኖ የሚደርስባቸዉ ነገሮች የትምህርት ይዘት ዝግጅት፣ የጊዜ አመዳደብ፣ በማስተማሩ ትኩረት የሚሰጣቸዉ ቦታዎች፣ የማስተማር ስነ-ዘዴ፣ የምርጃ መሳርያ ምርጫ፣ የክፍል ፈተና የአፈታተን ስልት እንደሆኑ ገልፀዋል፡፡ እነ Shohamy (1996) እንደሚያስረዱት ደግሞ በተለይ ከፍተኛ ዉሳኔ በሚወሰንባቸዉ ፈተናዎች ምክንያት ብዙ የማስተማር ጊዜ በክፍል ዉስጥ የፈተና ዝግጅት ላይ ይዉላል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ በፈተና ተፅዕኖ ምክንያት ብዙ የማስተማርያ ጊዜ ለሰፊ እዉቀት ሳይሆን ፈተናን ለማለፍ በሚደረግ ዝግጅት ላይ እንደሚጠፋ ነዉ፡፡

ሌላዉ በመማር ማስተማር ክንዉን በፈተና ተፅዕኖ የሚደርስበት የመርጃ መሳርያ ምርጫ ነዉ፡፡ በዚህ ዙርያ Spart (2005) በጥናታቸዉ ስለማጠናቀቂያ ፈተናዉ የሚጠቁሙ እና ከማጠናቀቂያ ፈተናዉ ጋር ግንኙነት ያላቸዉ መጽሐፍት እና የቀደሙት አመታት የፈተና ወረቀቶችን መምህራን በማስተማር ትግበራቸዉ ላይ እንደተጠቀሙባቸዉ ገልፀዋል፡፡ እንዲሁምSimachew(2012) መምህራን በአብዛኞቹ አጋጣሚዎች በማጠናቀቂያ ፈተናዉ ምክንያት በክፍል ዉስጥ መማር ማስተማር ትግበራቸዉ ላይ ከፈተናዉ ጋር ግንኙነት ካላቸዉ መርጃ መሳርያዎች ጥገኛ እንደሆኑ የተለያዩ ጥናቶች እንዳረጋገጡ ጠቁመዋል፡፡ Alderson እና Wall (1993) በጥናታቸዉ እንዲሁ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች መምህራን እና ተማሪዎች ከፈተናዉ ጋር የተያያዙ ወይም ለፈተናዉ የሚጠቅሙ ተጨማሪ መሳርያዎችን (materials) እንዲጠቀሙ እንደሚያደርጉ አሳይተዋል፡፡

Cheng (2002)፣ Shohamy (1996)፣ sprat (2005) እንደሚገልጹት መምህራን በማጠናቀቂያ ፈተና የሚካተቱ ወይም ሊካተቱ ይችላሉ ብለው የሚገምቷቸውን የትምህርት ክፍሎች የሚመለከቱ ተግባራትን የተለየ ትኩረት ሰጥተው ወይም የተሻለ ጊዜ መድበው ያስተምራሉ ብለዋል፡፡

## 2.1.10 በተማሪዎች ላይ የፈተና ወሽባክ ተጽዕኖዎች

አብዛኞች አጥኝዎች የፈተና ወሽባክ በተማዎች መማር ላይ ተጽዕኖ እንዳለው ይስማማሉ፡ ፡ Shih(2009) ሲገልጹ የጊዜ ድልደላ የመማር ይዘት እና የመርጃ መሳርያዎች በፈተና ተጽዕኖ ይደርስባቸዋል ብለዋል፡፡ የማጠናቀቂያ ፈተናው ወሽባክ ተማሪዎች የቋንቋውን ክሂል ለመማር በሚኖራቸው አመለካከት እና ተነሳሽነት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ይህን በተመለከተ አገኘሁ(2006) Shih(2007)ን ጠቅሰው እንደገለጹት ተማሪዎች ለፈተናው ያላቸው አመለካከት በመማር ትግበራቸው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል ብለዋል፡፡ ነገር ግን Cheng (1998) በዚህ አይስማሙም፡፡ ማለትም የማጠናቀቂያ ፈተናው ወሽባክ በተማሪዎች የመማር ትግበራ ላይ ተጽዕኖ እንደሌለው አሳይተዋል፡፡ "የሆንግ ኮንግ እንግሊዘኛ ፈተና በተማሪዎች መማር ላይ ያለው ወሽባክ" በተሰኘው ጥናታቸው የፈተናው ተጽዕኖ በተማሪዎች መማር ትግበራ ላይ ያለው ተጽዕኖ አነስተኛ እንደሆነ አረጋግጠዋል፡፡ ይሁን እንጅ አብዛኞቹ አጥኝዎች የፈተናው ወሽባክ በተማሪዎች መማር ላይ ተጽዕኖ እንዳለው ይስማማሉ፡፡ Alderson እና Wall (1993) የፈተና ወሽባክ በተማሪዎች መማር ስልት ላይ ተጽዕኖ እንዳለው ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም Aldersonእና Wall (1993) ካቀረቧቸው አስራ አምስት መላምቶች ውስጥ አምስቱ ተማሪዎችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

1. ፈተና በተማሪዎች መማር ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡
2. ፈተና ተማሪዎች እንዴት እንደሚማሩ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡
3. ፈተና በመማር መጠን እና ቅደም ተከተል ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡
4. ፈተና ተማሪዎች ምን እንደሚማሩ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡
5. ፈተና በመማር ደረጃ እና ጥልቀት ላይ ተጽዕኖ ለኖረው ይችላል የሚሉት ናቸው፡ ይህም የሚያሳየው የማጠናቀቂያ ፈተናው በተማሪዎች የመማር ፍላጎት እና የመማር ስልት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የማጠናቀቂያ ፈተናው ተማሪዎች ትምህርቱን ለመማር በሚያጠፉት ጊዜ እና ክንውን እንዲሁም ለመማር በሚመርጡት ይዘት ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶች መካከል አገኘሁ(2006) ጥናት አንዱ ነው፡፡ ይህ ጥናት የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ወሽባክ በሚል ርዕስ የተሰራ ነው፡፡ ጥናቱም ምልከታ፣ቃለ መጠይቅ፣የቡድን ውይይት ፣ሰነድ ፍተሻ መሳሪያዎችን በመጠቀም መረጃዎችን የሰበሰበ ሲሆን የተገኘው ውጤት እንዳመለከተውም በማጠቃለያ ፈተናዎች እና በአእምሯዊ ምድብ የትምህርት አላማዎች ፣በፈተናዎቹና በትምህርት ዓላማዎች ፣በቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችና በክፍል ውስጥ ፈተናዎች መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ የለም፡፡ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን ፣በተማሪዎችና በሌሎች የትምህርት ባለድርሻ አካላት ግንዛቤና ተግባራት ላይ በአብዛኛው ጠንካራ የሚባል ተጽዕኖ እያሳደረ ነው፡፡ ይህም የመማር ማስተማር ሂደቶቹ ፈተና ተኮር እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ በፈተናው ተጽዕኖ የሚደርስባቸው ዋናዋና የትምህርት ምድቦችም የትምህርቱ ተግባራት፣የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣የትምህርት ይዘቶችና የክፍል ምዘናዎች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ መምህራን ስለ ማስተማር ሙያና ስለፈተናው ጠቀሜታ ያላቸው ግንዛቤ፣በፈተናው ስለሚካተቱ ይዘቶች  ያላቸው እውቂያ ፣የተማሪዎች የመማር ዝንባሌ በመምህራን ላይ የሚያሳድረው ጫና ፣የጊዜው ማነስ፣ወዘተ ላቅ ያለ በአዛኛውም አሉታዊ የሆነ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

አንጓች (2011) የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ክልላዊ ፈተና በመምህራን የማስተማር ሂደት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ፍተሻ በሚል ርዕስ የተሰራ ሲሆን ዋና አላማውም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተና በጎንደር ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቤቶች በመምህራን የማስተማር ሂደት ያሳደረውን ተፅዕኖ መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ለማድረግም የተጠቀመችው ገላጭ የምርምር ንድፍን ነው፡፡ ጥናቱም ምልከታ፣ቃለ መጠይቅ፣የጽሁፍ መጠይቅ፣ሰነድ ፍተሻ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን የተጠቀመች ሲሆን የጥናቱ ተሳታፊዎች 8ኛ ክፍል ከሚያስተምሩና ካስተማሩት መምህራን መካከል ከአንድ ዓመት በላይ ያስተማሩትንና በማስተማር ላይ ያሉትን ብቻ አሳትፏል፡፡ በዚህ መሰረትም 51 መምህራን በዓላማ ተኮር ዘዴ በናሙናነት ተሳትፈዋል፡፡ ጥናቱ በጎንደር ከተማ አስተዳደር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተመሰረተ ሲሆን የከተማ አስተዳደሩ የተመረጠው በአመቺ ናሙና ነው፡፡ በከተማው ያሉ 17 የግልና 29 የመንግስት በድምሩ 46 ትምህርት ቤቶች በጠቅላይ ናሙና ዘዴ

መርጣለች፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤት በመጠናዊና በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ተተንትኗል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንዳመለከተው የስምንተኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በመምህራን የይዘት ምርጫ ፣የጊዜ አጠቃቀም፣የቁሳቁስ ምርጫ እና የክፍል ውስጥ ምዘና ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ በአንጻሩ ፈተናው በመምህራን የማስተማር ዘዴ ምርጫ ላይ ያለው ተጽዕኖ መካከለኛ አሉታዊ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያለው በYasin Hajo እ.ኤ.አ (2014) ላይ የተሰራው ጥናት ነው፡፡ የYasin ጥናት ‹‹የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእንገሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና በመምህራን የማስማር ትግበራ ላይ ያለው ተጽዕኖ ››በሚል ርዕስ የተሰራ ሲሆን ዋና አላማው የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የማስተማር ትግበራ ላይ ያለውን ተጽዕኖ መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ለማድረግም ንጥል የጥናት ዘዴን (Case study ) ተጠቅሟል፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በሰነድ ፍተሻ በክፍል ምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ተሰብስቧል፡፡ የ2001 እና የ2005 የማጠናቀቂያ ፈተናዎች እንዲሁም በተለያዩ የቋንቋ መምህራን ለመጀመሪያው መንፈቅ ዓመት የተዘጋጁ የእንግሊዘኛ ቋንቋ የማጠናቀቂያ ፈተናዎች በጥናቱ ተዳሰዋል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የእንግሊዘኛ ቋንቋ መምህራን እና የ9ኛና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ጥናቱ መምህራንን በአመች የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተማሪዎችን ደግሞ በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ መርጧል፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤት በአይነታዊ የመረጃ መተነተኛ ዘዴ ተተንትኗል፡፡ የጥናቱ ውጤትም የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የማስተማር ትግበራ ላይ ጎጅ ተጽዕኖ እንዳሳደረ አሳይቷል፡፡

በማጠናቀቂያ ፈተናው ሰዋሰው እና ንባብ የበለጠ ትኩረት ተሰጥቷቸው ተገኝቷል፡፡ ይህ ተጽዕኖም መምህራን የሚያስተምሩት ይዘት በሰዋሰው እና በንባብ ላይ እንዲወሰን አድርጓል፡፡ ስለሆነም የማጠናቀቂያ ፈተናው ሰዋሰውን መሰረት ያደረገ በመሆኑ መምህራን ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ስነ ዘዴን ችላ እንዲሉ እና መምህር መራሽ የማስተማር ዘዴን እንዲከተሉ አድርጓቸዋል፡፡ ይህ ጥናት በወሽባክ ዙሪያ የተሰራ በመሆኑ ከYasin(2014)ጥናት ጋር ቢመሳሰልም ልዩነት አለው፡፡ የYasin ጥናት የሁለተኛ ደረጃ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የማስተማር ትግበራ ያሳደረውን ተጽዕኖ የሚፈትሽ ሲሆን ይህ ጥናት ግን የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በመምህራን እና በተማሪዎች ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ የሚመረምር ነው፡፡

እንዲሁም የYasin የተከተለው የጥናት ዘዴ ንጥል የጥናት ዘዴን  ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ቅይጥ የጥናት ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ ከዚህም ሌላ የYasin ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ የክፍል ምልከታን ፣ሰነድ ፍተሻን እና ቃለ መጠይቅን የተጠቀመ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ቃለ መጠይቅን ፣የጽሁፍ መጠይቅን ፣ የሰነድ ፍተሻ እና የክፍል ምልከታ ተጠቅሟል፡፡ በተጨማሪም የYasin ጥናት አላማ ተኮር እና አመች የናሙና አመራረጥ የተጠቀመ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ አመች፣ጠቅላይ እና ቀላል የእጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ በመረጃ የመተንተኛ ዘዴም የYasin ጥናት አይነታዊ የመተንተኛ ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ቅይጥ የመተንተኛ ዘዴን ተጠቅሟል፡፡ ስለሆነም  ይህ ጥናት ከYasin ጥናት ጋር ይለያያል፡፡

በተጨማሪም Simachew እ.ኤ.አ (2012) የ12ኛ ክፍል የእንግሊዘኛ ማጠቃለያ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና በመምህራን እና በተማሪዎች ትግበራ ላይ ያለው ተጽዕኖ በሚል ጥናት አድርገው ነበር፡፡ ለዚህም 62 የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል መምህራን በመረጃ ሰጭነት ተሳትፈውበታል፡፡ 1579 የተለያዩ የአማራ ክልል መሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎችም ተሳትፈውበታል፡፡

ተመራማሪው በጥናታቸው እንደገለጹትም የመምህራን የትምህርት አተገባበር በፈተናው ተጽዕኖ አድሮበታል፡፡ የማስተማር ትኩረቱ በቃላት፣በሰዋሰው እና በእውቀት ነክ የጽህፈት እና የመናገር ክሂሎች ላይ ሆኗል፡፡ የክፍል ውስጥ ምዘናውም ሆነ መማሩ ተግባቦታዊ በሆነው  የመርሃ ትምህርቱ መሰረት አይደለም፡፡ ሁሉም ፈተና ተኮር ሆኖ ይከናወናል፡፡ መምህራንም ሰፊ ጊዜያቸውን እነዚህን ይዘቶች በማስተማር ላይ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡

በአጠቃላይ የመምህራን የማስተማር ጥረት ተማሪዎች በፈተናው እንዲያልፉ እንጅ በመርሀ ትምህርቱ ላይ የቀረቡትን ተግባቦታዊ ክሂሎች እንዲያሳኩ አይደለም፡፡ የተማሪዎች የመማር አተገባበርም እንዲሁ በፈተናው ተጽዕኖ አድሮበታል፡፡ የተማሪዎች የትምህርት ይዘት ትኩረትም እንደ መምህሩ ቅርጽ ተኮር የቋንቋ ገጽታዎች ላይ ሆኗል፡፡

በአጠቃላይ የመምህሩ የትምህርት ይዘት ምርጫ እና የማስተማር ዘዴ በተማሪዎች የመማር ይዘት ምርጫ እና የመማር ልምምድ ላይ ተጽዕኖ አሳድሮበታል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በቸሃ ወረዳ የሚገኙ አራት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተማሪዎችና በመምህራን ላይ ያለዉ ተፅዕኖ መፈተሽ ነው። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ አጥኝዋ የተጠቀመችው ገላጭ የምርምር ንድፍን ነው። ይህም የምርምር ስልት የተመረጠበት ምክንያት ለጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎች በትረካ መልክ ስለሚተነተኑ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት የምርምር ንድፍ፣ መጠናዊና አይነታዊ ወይም ቅይጥ የመረጃ መተንተኛ ስልት ጋር ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

## 3.2 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

የዚህን ጥናት አላማ ከግብ ለማድረስ አጥኚዋ ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎችን በመሰብሰብ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን ጥቅም ላይ አውላለች። በመሆኑም ለዚህ ጥናት የመረጃ ምንጭ 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ፣ በ2013 ዓ.ም የሚማሩ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲሁም በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል በየአመቱ የሚዘጋጀው የ2011 ዓ.ም እና የ2012 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡

## 3.3 የንሞና አመራረጥ ዘዴ

በዚህ ጥናት የትምህርት ቤት፣ የመምህራን ፣ የተማሪዎች ንሞና መረጣ ተካሂዷል፡፡

### 3.3.1 የትምህርት ቤቶች ንሞና አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልል በጉራጌ ዞን በቸሃ ወረዳ ከሚገኙ ጠቅላላ ሃያ ሁለት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ  በአራቱ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ሲሆን ትምህርት ቤቶቹም በአመቺ የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ አመቺ ንሞና የተጠቀመችበት ምክንያት የአጥኚዋ የስራ ቦታ ከዚያው አካባቢ ስለሆነ ነው፡፡ የተመረጡት ትምህርት ቤቶችም የጆካ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣የሰስዬ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የጠናቃ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና እናቴ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው፡፡

### 3.3.2 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል በጉራጌ ዞን በቸሃ ወረዳ በሚገኙ አራት 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ውስጥ ማለትም የጆካ 2 መምህር፣ የሰስዬ1 መምህር፣ የጠናቃ 1 መምህር እና እናቴ 1 መምህር በጠቅላላ 5 መምህራን በጠቅላይ የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ አጥኚዋ ጠቅላይ ንሞና የተጠቀመችበት ምክንያት በአራቱም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ያሉ 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አምስት ብቻ ስለሆኑ ሁላቸውንም በጠቅላይ ንሞና ተመርጠዋል፡፡ በመሆኑም በአራቱም ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሁሉም 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጥናቱ ውስጥ ተተኳሪ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የተጠኙ መምህራን ብዛት አምስት ሲሆኑ አራት ሴት እና አንድ ወንድ ናቸው ፡፡ ሁሉም መምህራን በአማርኛ የትምህርት መስክ የተመረቁ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ውሰጥ አራቱ ቢ.ኤ ዲግሪ ያላቸው ሲሆን አንዱ ደግሞ ዲፕሎማ ነው ፡፡ አገልግሎታቸው ደግሞ ከሶስት እስከ ሰባት ዓመት ነው፡፡

### 3.3.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በአራቱም ትምህርት ቤት ከሚገኙት ጠቅላላ ተማሪዎች ሃያ ሃያ ፐርሰንት በናሙናነት ተመርጠዋል፡፡ በየጆካ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጠቅላላ የተማሪ ቁጥር 92 ሲሆኑ ለናሙና የተመረጡት 19 ተማሪዎች ፣በየሰስዬ ጠቅላላ የተማሪ ቁጥር 65 ሲሆኑ ለናሙና የተመረጡት ተማሪዎች 13 ፣የጠናቃ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጠቅላላ የተማሪ ቁጥር 74 ለናሙና የተመረጡት 15 ተማሪዎች፣እናቴ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጠቅላላ የተማሪ ብዛት 75 ለናሙና የተመረጡት ተማሪዎች ደግሞ 15 ናቸው፡፡ በአራቱ ትምህርት ቤቶች እና በየትምህርት ቤቱ ሃያ ሃያ ፐርሰንት የተመረጡት ያለው እንዳወቅ (2009) “ተመራማሪው ጥናቱን የሚያካሂድበት የጥናቱ አካላይ በውስጡ ያቀፋቸው አባላቱ ተመሳሳይ ባህሪ ከኖራቸው በርካታ ቁጥር ያለው ናሙና መውሰድ አስፈላጊ አይሆንም” በማለት የገለፁትን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በጠቅላላው ከአራቱ ትምህርት ቤቶች 306 የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲኖሩ 62 ተማሪዎች በቀላል የእጣ ንሞና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የአንድን ጥናት መረጃ ታማኒነት ፣አስተማማኝነት እና ትክክለኛነት ከሚወስኑት በጣም አስፈላጊ ነገሮች መካከል የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛሉ፡ ፡እንደ ጥናቱ ሂደት እና አይነት እንደ ተጠኝዎች ሁኔታ ፣እንደ አጥኝዋ ችሎታ ፣ጥናቱን ለማካሄድ እንዳላት የጊዜ እና የገንዘብ መጠን ለመረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግሉ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አሉ፡፡ በመሆኑም ሰነድ ፍተሻ፣ የጽሁፍ መጠየቅ ፣ ቃለመጠይቅ እና የክፍል ውስጥ ምልከታ ተግባር ላይ ውለዋል፡፡

### 3.4.1 ሰነድ ፍተሻ

ይህ ጥናት የማጠናቀቂያ ፈተና ወሸባክን በሚመለከት የተካሄደ ነው፡፡ የማጠናቀቂያ ፈተናውን ተጽዕኖ ለመመርመር ደግሞ የማጠናቀቂያ ፈተናውን መፈተሽ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም ፈተናው በየትኛው የቋንቋ ትምህርት ይዘት ላይ በስፋት ትኩረት ሰጥቶ እንደ ተዘጋጀ እና ምን ምን ይዘቶችን አካቶ ቀርቧል የሚለውን ለመመርመር የ2011 ዓ.ም እና የ2012 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል የመጀመሪያ ደረጃ ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና በአላማ ተኮር ናሙና ተመርጠዋል፡፡ እነዚህ የሁለት ተከታታይ አመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች የተመረጡበት ምክንያት አሁን በስራ ላይ ያለው መፅሀፍ ከታተመ በኋላ የወጡ ፈተናዎች ስለሆኑ ነው፡፡

### 3.4.2 የፅሁፍ መጠይቅ

በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋለው ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የጽሁፍ መጠይቅ ነው ፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ 23 ነጥቦችን የያዘ ሲሆን (Bailey, 1999) ንድፍ መሰረት በማድረግ ከመጠነኛ ማሸሻያ ጋር ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል ፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ የተመረጠው የጥናቱን አላማ የሚመለከት በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ከ1 -11 የማጠናቀቂያ ፈተናው በተማሪዎች መማር ላይ ያለው ተፅዕኖ ፣ ከ12-19 የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴ እና ትግበራቸው ላይ ያለው ተፅዕኖ ፣ ከ20-23 የክፍል ውስጥ ተግባራትን በተመለከተ የቀረቡ ናቸው ፡፡ ዝግ የጽሁፍ መጠይቁ አምስት ነጥብ (በሊከርት ስኬል) ያለው ሲሆን ይህም ከ1 (በጣም አልስማማም) እስከ 5 (በጣም እስማማለሁ) የተዘጋጁ የምርጫ ወይም ዝግ ጥያቄዎች ያካተተ ነው ፡፡

### 3.4.3 ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ ሌላው መረጃ መሰብሰቢያ መንገድ ሲሆን ተፅዕኖውን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ከመምህራን ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ አላማውም ክልላዊ ፈተናው በመምህራን ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ ለማወቅ ነው፡፡ የጥያቄዎች ብዛትም 10 ሲሆኑ መጠይቁ የተካሄደው በጠቅላይ ናሙና በተመረጡ አምስት መምህራን ላይ ነው፡፡ የትምህርት ቤቶች አመራረጥ በተመለከተ በአራት ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በአመች ናሙና በመምረጥ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ እነዚህ መረጃ ሰጭዎች በክፍል ውስጥ ምልከታውም ተጠንተዋል፡፡

### 3.4.4. የክፍል ውስጥ ምልከታ

የጥናቱ ዋና አላማ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በቸሃ ወረዳ በተመረጡ አራት 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመምህራን እና በተማሪዎች ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ መፈተሽ ነው፡፡ ምልከታው ያልተዋቀረ ምልከታ ነው ፡፡ ምልከታው ከአንድ ሁለተኛ ዲግሪ ያለው መምህር ከአጥኝዋ ጋር ተጨምሮ ለሁለት እንዲከናወን ተደርጓል፡፡ ምልከታው ቀድሞ ትኩረት የሚደረግባቸውን ነጥቦች ከጥናቱ አላማ አንፃር በመለየት እና በክፍል ውስጥ የታዩ ተየያዥ ጉዳዮች ትምህርት በሚሰጥበት ጊዜ በክፍል ውስጥ በመገኘት ተከናውኗል ፤ ምልከታውም በአጥኝዋ እና አንድ ሁለተኛ ዲግሪ ባለው በአንድ ሌላ ሰው የተካሄደ ሲሆን በዋናነት ትምህርት ክዋኔዎችን እንዳቀራረባቸው በማስታወሻ በመያዝ መረጃው ተሰብስቧል፡፡ ምልከታውም በአምስቱ መምህራን ለእያንዳንዱ መምህር በተከታታይ ለሁለት ጊዜ አጠቃላይ አስር ምልከታዎች ተካሂደዋል፡፡ ያልተዋቀረ ምልከታ ማድረጉን አጥኝዋ እና አማካሪዋ ተወያይተው ተገቢነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ለዋናው ስራ የዋለ ነው።

## 3.5 የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

በዚህ ጥናት በአራቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ማለትም በሰነድ ፍተሻ፣ በጽሁፍ መጠይቅ ፣ቃለ መጠይቅ እና በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኙ መረጃዎች እንደ አመችነታቸው በአይነታዊ እና በመጠናዊ (ቅይጥ) የመተንተኛ ስልቶች ተተንትነዋል፡፡ በመሆኑም በቃለ መጠይቅ እና በክፍል ውስጥ ምልከታ የተሰበሰቡት መረጃዎች በአይነታዊ ዘዴ የተተነተኑ ሲሆን በሰነድ ፍተሻ እና በዝግ የጽሁፍ መጠይቅ ከተማሪዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በመጠናዊ መተንተኛ ስልት ተተንትነዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት ፣ የመረጃ ትንተና እና ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በቾሃ ወረዳ የሚገኙ አራት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመምህራንና በተማሪዎች ላይ ያለው ተፅዕኖ መፈተሽ ሲሆን መሰረታዊ ጥያቄዎቹ ደግሞ፤ የ2011 ዓ.ም እና የ2012 ዓ.ም የደቡብ ክልል የ8ኛ ክፍል ፈተና የይዘት ስርጭት ምን ይመስላል? የ8ኛ ክልላዊ ፈተናው በመምህራን የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴና ትግበራቸው ላይ የሚየሳድረው ተፅዕኖ ምንድን ነው? የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በክፍል ውስጥ ፈተና ዝግጅትና ስልት ላይ ያለው ተፅዕኖ ምንድን ነው? በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ምክንያት የተከሰቱ አዎንታዊ እና አሉታዊ ተፅዕኖዎች ምንምን ናቸው? የሚሉ ነበሩ፡፡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ዓይነታዊ መረጃ በትረካ የተገለፀ ሲሆን መጠናዊ መረጃዎች ደግሞ በመቶኛ ተተንትኗል፡፡

በዚህ ክፍል የ2011 ዓ.ም እና የ2012 ዓ.ም የደቡብ ክልል 8ኛ ክፍል ፈተና የይዘት ስርጭት ፣ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በተማሪዎች መማር ላይ ያለው ተፅዕኖ ፣ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በመምህራን የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴና ትግበራቸው ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ፣ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በክፍል ውስጥ ፈተና ዝግጅትና ስልት ላይ ያለው ተፅዕኖ ፣ በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ምክንያት የተከሰቱ አወንታዊ እና አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለመፈተሽ በአራት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ ከሰነድ ፍተሻ ፣ከጽሁፍ መጠይቅ ፣ ከቃለ መጠይቅና ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ከጥናቱ አበይት ጥያቄዎች አኳያ በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የጥናቱ የመጀመሪያ መሪ ጥያቄ "የ2011 ዓ.ም እና የ2012 ዓ.ም የደቡብ ክልል የ8ኛ ክፍል ፈተና ያካተታቸው ይዘቶች ምንምን ናቸው?" የሚል ሲሆን በሰነድ ፈተሻ የተገኘው መረጃ በቁጥርና በመቶኛ ቀጥለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## ሰንጠረዥ4. 1 የ2011 ዓ.ም እና የ2012 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ክልላዊ የማጠናቀቂያ ፈተና የይዘት ስርጭት

| የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች | 2011ዓ.ም የጥያቄዎች ብዛት | | የ2012 ዓ.ም የጥያቄዎች ብዛት | |
|---|---|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| የማንበብ ክሂል | 18 | 30 | 25 | 41.67 |
| የመጻፍ ክሂል | 14 | 23.33 | 11 | 18.33 |
| የንግግር ክሂል | 5 | 8.33 | 3 | 5 |
| የማዳመጥ ክሂል | 0 | 0 | 1 | 1.67 |
| ቃላት | 10 | 16.67 | 10 | 16.67 |
| ስነ-ጽሁፍ | 7 | 11.67 | 4 | 6.67 |
| ሰዋስው | 6 | 10 | 6 | 10 |
| ድምር | 60 | 100 | 60 | 100 |

ከላይ በሰንጠረዥ4.1 ስር እንደገለፀው በ2011 ዓ.ም በተዘጋጀው የ8ኛ ክፍል የማጠናቀቂያ ፈተና ላይ የማንባብ ክሂል አስራ ስምት ጥያቄዎች (30%) ፣የፅህፈት ክሂል አስራ አራት ጥያቄዎች (23.33%) ፣የንግግር ክሂል አምስት ጥያቄዎች (8.33%)፣የማዳመጥ ክሂል (0%) ፣ቃላት አስር ጥያቄዎች (16.67%) ፣ስነ-ፅሁፍ ሰባት ጥያቄዎች (11.67%) እና ሰዋሰው ስድስት ጥያቄዎች (10%) ሆነው ቀርበዋል፡፡

በ2012 ዓ.ም በተዘጋጀው የማጠናቀቂያ ፈተና ደግሞ የማንባብ ክሂል ሀያአምስት ጥያቄዎች (41.67%)፣ የፅህፈት ክሂል አስራ አንድ ጥያቄዎቸ (18.33%) ፣የንግግር ክሂል ሶስት ጥያቄዎች (5%) ፣የማዳመጥ ክሂል አንድ ጥያቄ (1.67%) ፣ቃላት አስር ጥያቄዎች (16.67%)፣ ስነ-ፅሁፍ አራት ጥያቄዎች(6.67%) እና ሰዋሰው ስድስት ጥያቄዎች (10%) በመሆን ቀርበዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው በሁለቱም ተከታታይ አመታት የማጠናቀቂያ ፈተናዎች የማንባብ ክሂል፣ የፅሀፈት ክሂል እና ቃላት ከፍተኛ ሽፋን ተሰጥቷቸው የተዘጋጁባቸው መሆኑን ነው፡፡ ለማንባብ ክሂል፣ ለፅህፈት ክሂል እና ለቃላት በሁለቱም ተከታታይ አመታት በቅደም ተከተል 71.67%፣ 41.66%፣ 33.34% ሽፋን ተሰጥቷቸዋል፡፡

ለማዳመጥ ክሂል፣ ለንግግር እና ለስነ-ፅሁፍ አነስተኛ ሽፋን ተሰጥቷቸዋል፡፡ እንዲሁም በ2011 ዓ.ም በተዘጋጀው የማጠናቀቂያ ፈተና የማዳመጥ ክሂል ምንም አይነት ሽፋን ሳይሰጣቸው ቀርቷል፡፡ ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናዎች ለሁሉም የቋንቋ ክሂሎች እና የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ተመጣጣኝ ውክልና ሰጥተው እንዳልተዘጋጁ ያሳያል፡፡ መምህራንም በቃለ መጠይቁ ወቅት የማጠናቀቂያ ፈተናው ለሁሉም የቋንቋ ክሂሎች እና ይዘቶች ተመጣጣኝ ውክልና ሰጥቶ እንዳልተዘጋጀ ገልፀዋል፡፡ ከዚህም ሌላ የማጠናቀቂያ ፈተናው ብዙም የማያተኩርባቸው ከመፅሀፉ ያሉ አንዳንድ ርዕሶችን ትዘላቸዋለህ/ሽ በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኞቹ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው የማያተኩርባቸው ርዕሶችን እንደሚዘሏቸው ገልፀዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው የመማሪያ መጽሀፉን ዓላማ መሰረት አድርጎ ከማስተማር ይልቅ በክልላዊ ፈተናው የተካተቱ የትምህርት ይዘቶች ላይ ተመስርተው እንደሚያስተምሩ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመማር ማስተማር ክንውን ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲያሳድር ሊያደርገው ይችላል፡፡

ለንግግር ክሂል እና ለማዳመጥ ክሂል አነስተኛ ሽፋን መስጠቱ እና በጭራሽ አለመካተቱ መምህራን ለማስተማር ትኩረት እንዳይሰጡት ያደርጋል፡፡ ተማሪዎችም ቢሆን ለመማር ፍላጎት እንዳይኖራቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡ መምህራን በቃለ መጠይቁ ላይ በፈተናው የማይካተቱ ይዘቶችን እንደሚዘሏቸው ተናግረዋል፡፡ ስለሆነም የማጠናቀቂያ ፈተናው ለሁሉም ይዘቶች እኩል ሽፋን ባለመሰጠቱ በመማር ማስተማሩ ክንውን ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል ማለት ነው፡፡

የጥናቱ ሁለተኛ መሰረታዊ ጥያቄ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናው በተማሪዎች መማር ላይ ያለው ተፅዕኖ ምን ይመስላል? የሚለው ሲሆን ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃም ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ 4.2 ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.2 የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናው በተማሪዎች መማር ላይ ያለው ተፅዕኖ በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎችና ትንተና**

| ተ.ቁ | የመጠይቅ ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በ.አ | | አ. | | ለ.እ | | እ. | | በ.እ | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 1 | የማጠናቀቂያ ፈተናው ትኩረት በሚያደርግባቸው ይዘቶች ላይ ብቻ ትኩረት አድርጌ አነባለሁ | 6 | 9.7 | 15 | 24.2 | 6 | 9.7 | 20 | 32.2 | 15 | 24.2 |
| 2 | አንዳንድ ይዘቶች በማጠናቀቂያ ፈተናው ባይካተቱም ሁሉንም ይዘቶች አካትቼ ለማንበብ ጥረት አደርጋለሁ | 6 | 9.7 | 10 | 15.2 | 5 | 8 | 17 | 27.4 | 24 | 38.7 |
| 3 | በክፍል ውስጥ የምማረው ክልላዊ ፈተናውን ለመስራት የሚያስችሉ ክሂሎችን እንዲያጎለብቱ የሚያግዙኝን ነው | 3 | 4.8 | 4 | 6.4 | 11 | 17.7 | 30 | 48.4 | 14 | 22.5 |
| 4 | የመማሪያ መጽሀፉ በቂ እና ለክልላዊ ፈተናው የሚያዘጋጁ መልመጃዎች እንዳሉት አስባለሁ | 14 | 22.6 | 19 | 30.6 | 12 | 19.3 | 9 | 14.5 | 8 | 12.5 |
| 5 | የመማሪያ መጽሀፉ ለክልላዊ ፈተናው ትኩረት ሰጥቼ አላነበውም | 8 | 12.9 | 18 | 29 | 5 | 8 | 21 | 33.8 | 12 | 19.4 |
| 6 | ከክልላዊ ፈተናው ጋር | 2 | 3.22 | 7 | 11.27 | 7 | 11.29 | 33 | 53.22 | 13 | 20.96 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ግንኙነት ባላቸው የፈተና ሸቶች ላይ ጥገኛ ነኝ | | | | | | | | | | |
| 7 | ሁሉንም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያሉትን የትምህርት ይዘቶች ባጠና ዝቅተኛ ውጤት ላስመዘግብ እችላለሁ | 21 | 33.87 | 18 | 29 | 4 | 6.45 | 8 | 12.67 | 11 | 17.74 |
| 8 | የክልላዊ ፈተናው ምን አይነት አጋዥ መጽሀፎችን ማንበብ እንዳለብኝ ተፅዕኖ አሳድሮብኛል | 8 | 12.9 | 11 | 17.7 | 11 | 17.7 | 17 | 27.4 | 15 | 24.2 |
| 9 | ከቋንቋ ክሂሎች ይልቅ ለሰዋሰዋዊ ይዘቶች ትኩረት ሰጥቼ በክፍል ውስጥ እከታተላለሁ | 10 | 16.1 | 12 | 19.4 | 8 | 12.9 | 22 | 35.4 | 10 | 16.1 |
| 10 | በማጠናቀቂያ ፈተናው ይመጣሉ ብዬ የማስባቸውን መልመጃዎች ትኩረት ሰጥቼ እሰራቸዋለሁ | 3 | 4.8 | 2 | 3.22 | 1 | 1.61 | 19 | 30.6 | 37 | 59.6 |
| 11 | የክልላዊ ፈተናው በምርጫ መልክ መቅረቡ የቋንቋ ችሎታዬን ለማሻሻል ጥረት እንዳላደርግ ገድቦኛል የሚል ሀሳብ አለኝ | 19 | 30.64 | 13 | 20.96 | 19 | 30.64 | 10 | 16.12 | 1 | 1.61 |

ከላይ በሰንጠረዥ 4.2 የቀረበው መረጃ ክልላዊ ፈተናው በተማሪዎች መማር ስልት ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ የሚመለከት ነው፡፡በመሆኑም እያንዳንዳቸው ጥያቄዎች እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ክልላዊ ፈተናው ትኩረት በሚያደርግባቸው ይዘቶች ላይ ብቻ ትኩረት ሰጥተው ማንበባቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ 6 ተማሪዎች (9.7%) በጣም አልስማማም ሲሉ 15 ተማሪዎች (24.2%) አልስማማም ብለዋል፡፡6 ተማሪዎች (9.7%) ለመወሰን እቸገራለሁ ሲሉ 20 ተማሪዎች (32.2%) እስማማለሁ በማለት የመለሱ ሲሆን ሌሎች 15 ተማሪዎች (24.2%) ደግሞ በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ ስለሆነም አብዛኞቹ ተመሪዎች (56.4%) በሀሰቡ እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡ተማሪዎች ክልላዊ ፈተናው ትኩረት በሚያደርግባቸው ይዘቶች ላይ ብቻ ትኩረት ሰጥተው የሚያነቡ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

አንዳንድ ይዘቶች በክልላዊ ፈተናው ባይካተቱም ሁሉንም ይዘቶች አካተው ለማንበብ ጥረት ማድረጋቸውን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች 6 ተማሪዎች (9.7%) በጣም አልስማማም በማለት የመለሱ ሲሆን 10 ተማሪዎች (15.2%) አልስማማም ብለዋል፡፡ 5 ተማሪዎች ለመወን እቸገራለሁ ሲሉ ሌሎች 17 ተማሪዎች (27.4%) እስማማለሁ ብለዋል፡፡ 24 ተማሪዎቾ (38.7%) በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (66.1%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ እና አንዳንድ ይዘቶች በክልላዊ ፈተናው ባይካተቱም ሁሉንም ይዘቶች አካተው ለማንበብ ጥረት እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡ ይህም አወንታዊ ወሽባክን ያመለክታል፡፡

በክፍል ውስጥ የሚማሩት የክልላዊ ፈተናውን ለመስራት የሚያስችሉ ክሂሎችን እንዲያጎለብቱ የሚያግዛቸው መሆኑን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ 3 ተማሪዎች (4.8%) በጣም አልስማማም ሲሉ 4 ተማሪዎች (6.4%) አልስማማም ብለዋል፡፡ 11 ተማሪዎች (17.7%) ለመወሰን እቸገራለሁ ሲሉ 30 ተማሪዎች (48.4%) እስማማለሁ ብለዋል፡፡ 14 ተማሪዎች ደግሞ (22.5%) በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ ስለሆነም ብዙዎች ተማሪዎች (70.9%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ተማሪዎች ክፍል ውስጥ የሚማሩት የክልላዊ ፈተናውን ለመስራት የሚያስችሉ ክሂሎችን እንዲያጎለብቱ የሚያስችላቸውን መሆኑን ነው፡፡

የመማሪያ መጽሀፉ በቂ እና ለክልላዊ ፈተናው የሚያዘጋጁ መልመጃዎች እንዳሉት ማሰባቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ 14 ተማሪዎች (22.6%) በጣም አልስማማም ብለዋል፡፡ እንዲሁም 19 ተማሪዎች (30.6%) አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ 12 ተማሪዎች (19.3%) ለመወሰን እቸገራለሁ ሲሉ ሌሎች 9 ተማሪዎች (14.5%) እስማማለሁ በማለት ሲመልሱ 8 ተማሪዎች (12.5%) በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ ስለሆነም አብዛኞቹ ተማሪዎች (53.2%) በሀሳቡ እንደማይስማሙ ገልፀዋል፡፡ይህም የሚያመለክተው የመማሪያ መጽሀፉ በቂ የሆነ እና ለክልላዊ ፈተናው የሚያዘጋጁ መልመጃዎች የሌሉት እንደሆነ የገለፁ ሲሆን በቃለ መጠይቅ ከተገኘው መረጃጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡ ከመማሪያ መጽሀፉ በሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መረጃ ጋር ግን አይደጋገፍም፡፡

የመማሪያ መጽሀፉን ለክልላዊ ፈተናው ትኩረት ሰጥተው የማያነቡት መሆኑን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ 8 ተማሪዎች (12.9%) በጣም አልስማማም በማለት ሲመልሱ 18 ተማሪዎች (29%) ደግሞ አልስማማም ብለዋል ፡፡ 5 ተማሪዎች (8%) ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል፡፡ 21 ተማሪዎች (33.8%) እስማማለሁ ሲሉ 12 ተማሪዎች (19.4%) በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ በመሆኑም አብዛኞቹ ተማሪዎች (53.2%) የመማሪያ መጽሀፉን ለክልላዊ ፈተናው ትኩረት ሰጥተው እንደማያነቡት ያሳያል፡፡ መምህራንም በቃለ መጠይቁ ወቅት ተማሪዎች የመማሪያ መጽሀፉን ትኩረት ሰጥተው እንዲያነቡ የማያበረታቱ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ምክንያታቸውም የመማሪያ መጽሀፉ ተማሪዎችን ለክልላዊ ፈተናው ለማዘጋጀት በቂ እንዳልሆነ ገልፀዋል ፡፡

ከክልላዊ ፈተናው ጋር ግንኙነት ካላቸው ሰነዶች ላይ ጥገኛ መሆናቸውን በተመለከተ ለቀረበ ጥያቄ 2 ተማሪዎች (3.22%) በጣም አልስማማም ብለዋል ፡፡7 ተማሪዎች (11.29%) እንዲሁ አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ 7 ተማሪዎች (11.29%) ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል፡፡ 33 ተማሪዎች (53.22%) እስማማለሁ ሲሉ 13 ተማሪዎች (20.96%) ደግሞ በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (74.18%) በሀሳቡ የሚስማሙ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ ስለሆነም አብዛኞቹ ተማሪዎች ከቀደሙት አመታት የፈተና ወረቀቶች ፣ሞዴል ፈተናዎች ወዘተ ጥገኛ እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ክልላዊ ፈተናው በተማሪዎች መማር ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ መምህራንም ተማሪዎች በክልላዊ ፈተናው የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ

ለክልላዊ ፈተናው የሚያግዙ መጽሃፎችን እንደሚጠቁሙ ተናግረዋል፡፡ የተለያዩ አመታት የፈተና ወረቀቶችንም እንደሚሰሩ በክፍል ምልከታው ተስተውሏል፡፡

ሁሉንም የመማሪያ መጽሀፉን ይዘቶች ቢያጠኑ ዝቅተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ መሆኑን በተመለከተ ጥያቄ 21 ተማሪዎች (33.87%) በጣም አልስማማም ሲሉ 18 ተማሪዎች (29%) አልስማማም ብለዋል፡፡ 4 ተማሪዎች (16.45%) ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል፡፡ ሌሎች 8 ተማሪዎች (12.67%) እስማማለሁ ሲሉ 11 ተማሪዎች (17.74%) በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ ስለሆነም አብዛኞቹ ተማሪዎች (62.87%) በሀሳቡ እንደማይስማሙ ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ ሁሉንም የመማሪያ መጽሀፉን ይዘቶች ቢያነቡ ዝቅተኛ ውጤት እንደማያመጡ መረዳት ይቻላል፡፡

ለክልላዊ ፈተናው ምን አይነት አጋዥ መጽሀፎችን ማንበብ እንዳለባቸው ተፅዕኖ ያሳደረባቸው መሆኑን ለመለየት የቀረበ ጥያቄ 8 ተማሪዎች (12.9%) በጣም አልስማማም ሲሉ 11 ተማሪዎች (17.7%) አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ 11 ተማሪዎች (17.74%) ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ ሌሎች 17 ተማሪዎች (27.4%) እስማማለሁ ሲሉ 15 ተማሪዎች (24.2%) ደግሞ በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (51.6%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡ ክልላዊ ፈተናው በአጋዥ መጽሀፍ ምርጫቸው ላይ ተፅዕኖ ያሳደረ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በቃለ መጠይቁም መምህራን ክልላዊ ፈተናው በመርጃ መሳሪያ ምርጫቸው ላይ ተፅዕኖ እንዳሳደረባቸው እና ለክልላዊ ፈተናው የሚረዱ መጽሀፎችን እንደሚጠቀሙ ተናግረዋል፡፡ በምልከታውም ይህ ተስተውሏል፡፡ በአጠቃላይ ክልላዊ ፈተናው በተማሪዎች የአጋዥ መጽሀፍ ምርጫ ትኩረት በሚሰጡት የትምህርት ይዘት ላይ ተፅዕኖ ያሳደረ መሆኑን ጥናቱ ያመለክታል፡፡

ከቋንቋ ክሂሎች ይልቅ ለሰዋሰዋዊ ይዘቶች ትኩረት ሰጥተው በክፍል ውስጥ የሚከታተሉ መሆኑን በተመለከተ ለቀረበ ጥያቄ 10 ተማሪዎች (16.12%) በጣም አልስማማም ሲሉ 12 ተማሪዎች (19.35%) አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ 8 ተማሪዎች (12.9%) ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል፡፡ ሌሎች 22 ተማሪዎች (35.4%) እስማማለሁ ሲሉ 10 ተማሪዎች (16.12%) ደግሞ በጣም እስማማለሁ ብለዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (51.52%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ከክሂሎች ይልቅ ለሰዋሰዋዊ ይዘቶች ትኩረት ሰጥተው እንደሚከታተሉ መረዳት ይቻላል፡፡

በክልላዊ ፈተናው ይመጣሉ ብለው የሚያስቧቸውን መልመጃዎች ትኩረት ሰጥተው የሚሰሩ መሆኑን በተመለከተ ለቀረበ ጥያቄ 3 ተማሪዎች (4.8%) በጣም አልስማማም ሲሉ 2 ተማሪዎች (3.2%) አልስማማም ብለዋል፡፡ 1 ተማሪ (1.61%) ለመወሰን እቸገራለሁ ብሏል፡፡ ሌሎች 19 ተማሪዎች (30.64%) እስማማለሁ ሲሉ 37 ተማሪዎች (59.67%) በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (90.2%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በክልላዊ ፈተናው ይመጣሉ የሚሏቸውን መልመጃዎች በትኩረት እንደሚሰሩ ነው፡፡

ክልላዊ ፈተናው በምርጫ መልክ መቅረቡ ጥረት እንዳያደርጉ ያደረጋቸው መሆኑን በተመለከተ ለቀረበ ጥያቄ 19 ተማሪዎች (30.64%) በጣም አልስማማም ሲሉ 13 ተማሪዎች (20.96%) አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ 19 ተማሪዎች (30.64%) ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል፡፡ ሌሎች 10 ተማሪዎች (16.12%) እስማማለሁ ሲሉ 1 ተማሪ ደግሞ (1.61%) በጣም በማለት መልሰዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (51.6%) በሀሳቡ እንደማይስማሙ ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ክልላዊ ፈተናው በምርጫ መልክ መቅረቡ ጥረት እንዳያደረጉ ያልገደባቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ሶስተኛው የጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄ “የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናው በመምህራን የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴና ትግበራቸው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ምን ይመስላል?” የሚለው ነው፡፡ በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃም በሚቀጥለው ሰንጠረዥ 4.3 ቀርቧል፡፡

## ሰንጠረዥ 4.3 የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናው በመምህራን የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴና ትግበራቸው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ትንተና

| ተ.ቁ | የመጠይቅ ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በ.አ | | አ. | | ለ.እ | | እ. | | በ.እ | |
| | | በቁ.. | በ% | በቁ.. | በ% | በቁ.. | በ% | በቁ.. | በ% | በቁ.. | በ% |
| 12 | መምህራችን በክልላዊ ፈተናው ዙሪያ ጥሩ ውጤት እንድናስመሰግብ የሚያስችሉ የማስተማሪያ ሁኔታዎችን ይጠቀማሉ | 4 | 6.45 | 5 | 8.06 | 3 | 4.83 | 30 | 48.38 | 20 | 32.25 |
| 13 | መምህራችን በክልላዊ ፈተናው የሚካተቱ የትምህርት ይዘቶችን ለማስተማር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ይጠቀማሉ | 4 | 6.45 | 4 | 6.45 | 8 | 12.9 | 25 | 40.32 | 21 | 33.8 |
| 14 | መምህራችን ክፍል ውስጥ የሚያስተምሩት የቋንቋ ትምህርት ይዘት በክልላዊ ፈተናው በተደጋጋሚ የቀረቡ ይዘቶችን ነው | 3 | 4.83 | 13 | 20.96 | 8 | 12.9 | 26 | 41.93 | 12 | 19.35 |
| 15 | መምህራችን ክፍል ውስጥ ንግግር እንድናደርግ ያበረታቱናል | 12 | 19.35 | 20 | 32.25 | 6 | 9.67 | 8 | 12.9 | 16 | 25.8 |
| 16 | መምህራችን የክልላዊ ፈተና ጥያቄዎችን እንዴት መመለስ እንዳለብን መመሪያ ይሰጡናል | 1 | 1.61 | 1 | 1.61 | 4 | 6.45 | 26 | 41.93 | 30 | 48.38 |
| 17 | መምህራችን የማስተማር አላማውን ቅደም ተከተል | 6 | 9.67 | 13 | 20.96 | 10 | 16.12 | 22 | 35.48 | 11 | 17.74 |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የሚያሲዙት በክልላዊ ፈተናው ላይ ተመስርተው ነው | | | | | | | | | | |
| 18 | መምህራን በክልላዊ ፈተናው የማይካተቱ የተወሰኑ የትምህርት ይዘቶችን ይዘሏቸዋል | 7 | 11.29 | 15 | 24.2 | 9 | 14.51 | 16 | 25.8 | 15 | 24.2 |
| 19 | መምህራን አንዳንድ ይዘቶች በማጠናቀቂያፈተናው ባይካተቱም ትኩረት ሰጥተው ያስተምራሉ | 8 | 12.9 | 14 | 22.58 | 7 | 11.29 | 17 | 27.41 | 16 | 25.8 |

ከላይ በሰንጠረዥ 4.3 በቀረበው መሰረት የክልላዊ ፈተናው በመምህራን የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴና ትግበራቸው ላይ ያሳደራቸውን ተፅዕኖ በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ ቀጥሎ ተተንትኖና ተብራርቶ ቀርቧል ፡፡

መምህራን ተማሪዎች በክልላዊ ፈተናው ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ የሚያስችሉ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎችን የሚጠቀሙ መሆኑን በተመከተ ለቀበላቸው ጥያቄ 4 ተማሪዎች (6.45%) በጣም አልስማማም ሲሉ 5 ተማሪዎች (8.06%) አልስማማም ብለዋል፡፡ 3 ተማሪዎች (4.83%) ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል፡፡ ከዚህም ሌላ 30 ተማሪዎች (48.38%) እስማማለሁ ሲሉ 20 ተማሪዎች (32.25%) በጣም እስማማለሁ ብለዋል፡፡ ስለሆነም አብዛኞቹ ተማሪዎች (80.63%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው መምህራን ለክልላዊ ፈተናው ብቁ የሚያደርጉ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ የሚፈልጉ መሆኑን ያሳያል፡፡ መምህራንም ተማሪዎችን ለክልላዊ ፈተናው ብቁ የሚያደርጉ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎችን እንደሚጠቀሙ በቃለ መጠይቁ ወቅት ተናግረዋል፡፡ መምህራን በክልላዊ ፈተናው የሚካተቱ የትምህርት ይዘቶችን ለማስተማር የሚያስችሉ ስነ-ዘዴዎችን ቢጠቀሙ የተሻለ እንደሆነ ለቀረበ ጥያቄ 4 ተማሪዎች (6.45%) በጣም አልስማማም ሲሉ 4ተማሪዎች (6.45%) እንዲሁ አልስማማም ብለዋል፡፡ 8 ተማሪዎች (12.9%) ደግሞ ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ 25 ተማሪዎች (40.32%) እስማማለሁ ሲሉ 21 ተማሪዎች (33.8%) ደግሞ በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ ስለሆነም አብዛኞቹ ተማሪዎች (74.12%) በሀሳቡ የተስማሙ ሲሆን ይህም የሚያሳየው

ተማሪዎቹ መምህራን በክልላዊ ፈተናው የሚካተቱ የትምህርት ይዘቶችን ለማስተማር የሚያስችሉ ስነ-ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ የሚፈልጉ መሆኑን ነው፡፡

መምህራን ክፍል ውስጥ በክልላዊ ፈተናው የቀረቡ የትምህርት ይዘቶችን ቢያስተምሩ የሚመርጡ መሆኑን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች 3 ተማሪዎች (4.83%) በጣም አልስማማም ሲሉ 13 ተማሪዎች (20.96%) አልስማማም ብለዋል፡፡ 8 ተማሪዎች (12.9%) ደግሞ ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ 26 ተማሪዎች (41.93%) እስማማለሁ ሲሉ 12 ተማሪዎች (19.35%) በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (61.28%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ተማሪዎች መምህራን ክፍል ውስጥ የሚያስተምሩት የቋንቋ ትምህርት ይዘት በክልላዊ ፈተናው ላይ የቀረበ ቢሆን የሚፈልጉ መሆኑን ነው፡፡

መምህራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንግግር እንዲያደርጉ የሚያበረታቱ መሆኑን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች 12 ተማሪዎች (19.35%) በጣም አልስማማም ሲሉ 20 ተማሪዎች (32.25%) አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ 6 ተማሪዎች (9.67%) ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል፡፡ ከዚህም ሌላ 8 ተማሪዎች (12.9%) እስማማለሁ ሲሉ 16 ተማሪዎች (25.8%) በጣም እስማማለሁ ብለዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (51.6%) በሀሳቡ እንደማይስማሙ እና መምህራን ተማሪዎቻቸውን በክፍል ውስጥ ንግግር እንዲያደርጉ የማያበረታቷቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

መምህራቸው የክልላዊ ፈተናውን እንዴት መመለስ እንዳለባቸው መመሪያ የሚሰጧቸው መሆኑን በተመለከተ ለቀረበ ጥያቄ 1 ተማሪ (1.61%) በጣም አልስማማም ሲል 1 ተማሪ (1.61%) እንዲሁ አልስማማም በማለት መልሷል፡፡ 4 ተማሪዎች (6.45%) ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል፡፡ ሌሎች 26 ተማሪዎች (41.93%) እስማማለሁ ሲሉ 30 ተማሪዎች (48.38%) በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (90.31%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው መምህራን ለተማሪዎቻቸው ክልላዊ ፈተናውን እንዴት መመለስ እንዳለባቸው መመሪያ የሚሰጧቸው መሆኑን ነው፡፡ መምህራን መማሪያ መጽሀፉን ከማስተማር ይልቅ የክልላዊ ፈተናውን እንዴት መመለስ እንደሚችሉ መመሪያ በመስጠት የትምህርት ጊዜያቸውን እንደሚያሳልፉ መረዳት ይቻላል፡፡

መምህራን የማስተማር አላማውን ቅደም ተከተል የሚያሲዙት በክልላዊ ፈተናው ላይ ተመስርተው መሆኑን በተመለከተ ለቀረበ ጥያቄ 6 ተማሪዎች (9.67%) በጣም አልስማማም ሲሉ 13 ተማሪዎች (20.96%) አልስማማም ብለዋል፡፡ 10 ተማሪዎች ደግሞ (16.12%) ለመወሰን እቸገራለሁ ብለዋል፡፡ ሌሎች 22 ተማሪዎች (35.48%) እስማማለሁ ሲሉ 11 ተማሪዎች (17.74%) በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (52.96%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡ስለዚህ መምህራን የማስተማር ዓላማውን ቅደም ተከተል የሚያሲዙት በመማሪያ መጽሀፉ መሰረት ሳይሆን የክልላዊ ፈተናውን መሰረት አድርገው እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

መምህራን በክልላዊ ፈተናው የማይካተቱ የተወሰኑ የትምህርት ይዘቶችን የሚዘሏቸው መሆኑን ለቀረበላቸው ጥያቄ 7 ተማሪዎች (11.29%) በጣም አልስማማም ሲሉ 15 ተማሪዎች (24.2%) አልስማማም ብለዋል፡፡ 9 ተማሪዎች (14.51%) ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ ሌሎች 16 ተማሪዎች (25.8%) እስማማለሁ ሲሉ 15 ተማሪዎች (24.2%) በጣም እስማማለሁ ብለዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (50%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ መምህራን በክልላዊ ፈተናው የማካይተቱ ይዘቶችን እንደሚዘሏቸው መረዳት ይቻላል፡፡

መምህራን አንዳንድ ይዘቶች በክልላዊ ፈተናው ባይካተቱም ትኩረት ሰጥተው የሚያስተምሩ መሆናቸውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ 8 ተማሪዎች (12.9%) በጣም አልስማማም ሲሉ 14 ተማሪዎች (22.58%) አልስማማም ብለዋል፡፡ 7 ተማሪዎች (11.29%) ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ 17 ተማሪዎች (27.41%) እስማማለሁ ሲሉ 16 ተማሪዎች (28.8%) በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (53.21%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡

## ሰንጠረዥ 4.4 የክፍል ውስጥ ተግባራትን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች እና ትንተና

| ተ.ቁ | የመጠይቅ ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በ.አ | | አ. | | ለ.እ | | እ. | | በእ. | |
| | | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 20 | ክፍል ውስጥ የ8ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተናው በብዛት ከሚተኮርበት የቋንቋ ትምህርት ይዘት ላይ ብዙ ጊዜ እናጠፋለን | 2 | 3.22 | 8 | 12.9 | 10 | 16.12 | 21 | 33.87 | 11 | 17.74 |
| 21 | የ8ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተናው ከመሰጠቱ በፊት አስቀድሞ ክፍል ውስጥ ሞዴል ፈተናዎችን እንሰራለን | 2 | 3.22 | 2 | 3.22 | 5 | 8.06 | 20 | 32.2 | 33 | 53.22 |
| 22 | በ8ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተናው ምክንያት ለቋንቋው ትምህርት አነስተኛ ትኩረት እንሰጣለን | 17 | 27.41 | 18 | 29 | 12 | 19.35 | 10 | 16.12 | 5 | 8.06 |
| 23 | ከ8ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ግንኙነት የሌላቸውን መልመጃዎች እና ተግባራት ችላ እንላቸዋለን | 20 | 32.25 | 15 | 24.2 | 10 | 16.2 | 9 | 14.51 | 8 | 12.9 |

*መግለጫ*

በ.አ = በጣም አልስማማም    አ = አልስማማም    ለ.እ = ለመወሰን እቸገራለሁ  እ = እስማማለሁ  በ.እ =  በጣም እስማማለሁ

ከላይ በሰንጠረዥ 4.4 በቀረበው መሰረት የክልላዊ ፈተናው በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተግባራት ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ በቀረቡ ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ ቀጥሎ ተተንትኖና ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ በክፍል ውስጥ የክልላዊ ፈተናው በስፋት ከሚተኮርባቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ላይ ብዙ ጊዜ የሚያጠፉ መሆኑን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄዎች 2 ተማሪዎች (3.22%) በጣም አልስማማን ሲሉ 8 ተማሪዎች (12.9%) አልስማማም ብለዋል፡፡ 10 ተማሪዎች (16.12%) ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ ሌሎች 21 ተማሪዎች (33.87%) እስማማለሁ ሲሉ 11 ተማሪዎች (17.74%) በጣም እስማማለሁ ብለዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (51.61%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በክፍል ውስጥ የክልላዊ ፈተናው በብዛት በሚተኮርባቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ላይ ብዙ ጊዜ የሚያጠፉ መሆኑን ነው ፡፡

የክልላዊ ፈተናው ከመሰጠቱ በፊት አስቀድሞ ክፍል ውስጥ ሞዴል ፈተናዎችን የሚሰሩ መሆኑን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ 2 ተማሪዎች (3.22%) በጣም አልስማማም ሲሉ 2 ተማሪዎች (3.22%) አልስማማም ብለዋል፡፡ 5 ተማሪዎች (18.06%) ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ 20 ተማሪዎች (32.2%) እስማማለሁ ሲሉ 33 ተማሪዎች (53.22%) በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (85.42%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው ክልላዊ ፈተናው ከመሰጠቱ አስቀድሞ  የተለያዩ ሞዴል ፈተናዎችን የሚሰሩ መሆኑን ነው፡፡ መምህራንም በቃለ መጠይቁ ተማሪዎች በክልላዊ ፈተናው የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡላቸው የተለያዩ ሞዴል ፈተናዎችን እና ያለፉ አመታት የክልላዊ ፈተና ወረቀቶችን እንደሚሰሩ ተናግረዋል፡፡

በክልላዊ ፈተናው ምክንያት ለቋንቋው ትምህርት አነስተኛ ትኩረት የሚሰጡ መሆኑን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ 17 ተማሪዎች (27.4%) በጣም አልስማማም ሲሉ 18 ተማሪዎች (29) አልሰማማም በማለት መልሰዋል፡፡ 12 ተማሪዎች (19.35%) ደግሞ ለመወሰን እንደሚቸገሩ ገልፀዋል፡፡ 10 ተማሪዎች (16.12%) እስማማለሁ ሲሉ 5 ተማሪዎች (8.06%) በጣም አልስማማም በማለት መልሰዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (56.4%) በሀሳቡ እንደማይስማሙ ገልፀዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው የክልላዊ ፈተናው ተማሪዎች ቋንቋቸውን ለመማር አነስተኛ ትኩረት እንዳይሰጡ ያደረጋቸው መሆኑን ነው፡፡

ይህ ደግሞ የክልላዊ ፈተናው በተማሪዎች ላይ የፈጠረው አዎንታዊ ተፅዕኖ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ከክልላዊ ፈተናው ጋር ግንኙነት የሌላቸውን መልመጃዎች እና ተግባራት ችላ የሚሏቸው መሆኑን በተመለከተ ለቀረበ ጥያቄ 20 ተማሪዎች (32.2%) በጣም አልስማማም ሲሉ 15 ተማሪዎች (24.2%) አልስማማም ብለዋል፡፡ 10 ተማሪዎች (16.2%) ለመወሰን እቸገራለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ 9 ተማሪዎች (14.51%) እስማማለሁ ሲሉ 8 ተማሪዎች (12.9%) በጣም እስማማለሁ በማለት መልሰዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች (56.45%) በሀሳቡ እንደማይስማሙ ገልፀዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው ተማሪዎች በክልላዊ ፈተናው የማይካተቱ መልመጃዎችንና ተግባራትን ክፍል ውስጥ ችላ እንደማይሏቸው ገልፀዋል፡፡ መምህራንም በቃለ መጠይቁ በክልላዊ ፈተናው የማይካተቱ መልመጃዎችን እና ተግባራትን ችላ እንደሚሏቸው ተናግረዋል፡፡ ይህም ተማሪዎች ከሞሉት ጋር የሚጣረስ ነው፡፡

## ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በመምህራን የክፍል ውስጥ የማስተማር ስነ-ዘዴ ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች መምህራን የሰጡት ምላሽ ተተንትኖና ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናው የተግባቦት የቋንቋ ትምህርትን እንዳይተገብሩ ተፅዕኖ ያሳደረባቸው መሆኑንና ያሳደረባቸው ተፅዕኖ ጥቅምና ጉዳት እንዲገልፁ ለቀረበ ጥያቄ አምስቱም መምህራን አዎ ጉዳት ነው በማለት መልሰዋል፡ ፡ምክንያቱም የመማሪያ መፅሀፉ ያለው ይዘትና በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚወጣው ከመማሪያ መፅሀፉ ውጭ ከሌሎች አጋዥ መጽሀፍትም እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ የመማሪያ መፅሀፉ የተግባቦት የቋንቋ ትምህርትን የሚጋብዝ ቢሆንም የማጠናቀቂያ ፈተናው ግን ብዙውን ጊዜ ከመማሪያ መፅሀፉ ጋር ተመስርቶ የማይዘጋጅ በመሆኑ ከመማሪያ መፅሀፉ ውጭ ያሉ የተለያዩ ይዘቶችን ከተለያዩ አጋዥ መፅሀፍት በማምጣት መምህር ተኮር የማስተማር ስነ-ዘዴን እንዲተገብሩ እንዳደረጋቸው ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም ክልላዊ ፈተናው የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን ስለሚዳስስና አብዛኞቹ ጥያቄዎች ከመማሪያ መፅሀፉ ውጭ ስለሆኑ መምህራንም የተለያዩ ይዘቶችን ከተለያዩ አጋዥ መፅሀፎች በማምጣት ለተማሪዎቻቸው እንደሚያስተምሩ ተናግረዋል፡፡ እንዲሁም ክልላዊ ፈተናው ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎች እኩል መጠን አካቶ የማይዘጋጅ በመሆኑና ብዙውን ጊዜ ንባብና መፃፍ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ያንን መሰረት አድርገው የሚያስተምሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በክፍል ውስጥ ለማስተማሪያነት የሚመርጡት የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ምን እንደሆነ ለቀረበ ጥያቄ ደግሞ የሰጡት ምላሽ ተማሪዎችን በማጠናቀቂያ ፈተናው ብቁ ያደርጓቸዋል ብለው የሚያስቧቸውን የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎች ነው፡፡ ለምሳሌ ገለፃ ፣ጥያቄና መልስ እንደሚመርጡ ተናግረዋል፡፡ በክልላዊ ፈተናው የሚካተቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን ለማስተማር የሚየስችሉ ማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎችን እንደሚያዘወትሩም አንስተዋል፡፡ መምህር ተኮር የማስተማር ስነ-ዘዴ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ለተማሪዎች ማስተዋሻ ለመስጠት ፣ገለፃ ለማድረግና ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ስነ-ዘዴን ለመተግበር ጊዜ ስለሚያንሳቸው እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው መምህራን ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎችና የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ለማስተማር የተለያዩ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎችን እንደማይጠቀሙ ነው፡፡ ማለትም በጥናቱ የተገኘው መረጃ በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚካተቱ የትምህርት ይዘቶችንና የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር የሚያግዙ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎችን ብቻ እንደሚጠቀሙ የሚያመለክት ነው፡፡ ተማሪዎችን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ብቁ የማያደርጉ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎችን ክፍል ውስጥ እንደማይጠቀሙ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴዎችን የሚመርጡት እና የሚተገብሩት ክልላዊ ፈተናው ለስኬት የሚያበቁ ስነ-ዘዴዎችን እንደሆነ ነው፡፡ ስለሆነም ክልላዊ ፈተናው በመምህራን የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ላይ ተፅዕኖ ያሳደረ እንደሆነና መምህራን ቋንቋውን ለማስተማር የሚጠቀሙት የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለስኬት ያበቃቸዋል ብለው የሚያስቡትን ስነ-ዘዴ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

## 4.5.የማጠናቀቂያ ፈተናው መምህራን በክፍል ውስጥ በሚያዘጋጇቸው ፈተናዎች ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ትንተና

በማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅዕኖ ከሚደርስባቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያዘጋጁት ፈተና ነው፡፡ ስለሆነም የማጠናቀቂያ ፈተናው መምህራን በክፍል ውስጥ በሚያዘጋጁት ፈተና ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ዙሪያ መምህራን የሰጡት ምላሽ ቀጥሎ ተተንትኖ እና ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ የ8ኛ ክፍል የማጠናቀቂያ ፈተናው በክፍል ውስጥ ፈተናቸው ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድርባቸው መሆኑንና ተፅዕኖው ምን እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ አራቱ መምህራን የማጠናቀቂያ ፈተናው በክፍል ውስጥ በሚያዘጋጇቸው ፈተናዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳሳደረባቸው ገልፀዋል፡፡ ይህም የማጠናቀቂያ ፈተናውን የሚመስሉ ጥያቄዎች እንዲፈትኑ ተፅዕኖ ያሳደረባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ጥያቄዎችን ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ለማመሳሰል ጥረት እንደሚያደርጉ ተናግረዋል፡፡ በክፍል ውስጥ ፈተናቸው ብዙ ጊዜ ጥያቄዎችን የሚያካትቱ ከማጠናቀቂያ ፈተናው እንደሆነም ገልፀዋል፡፡ ተማሪዎች ስለማጠናቀቂያ ፈተናው ግንዛቤ እንዲኖራቸው በተለያየ ዓመት ከማጠናቀቂያ ፈተናው የተካተቱ ይዘቶችን መሰረት አድርገው በዛው ስልት ጥያቄዎችን እንዲያዘጋጁ እንዳደረጋቸውም ገልፀዋል፡፡ ከዚህም ሌላ በፈተና በሚያካትቱት ይዘት እና የጥያቄ አወጣጣቸው ላይ ተፅዕኖ እንዳሳደረባቸው ጠቅሰዋል፡፡ ስለሆነም መምህራን ክፍል ወስጥ ተማሪዎቻቸውን የሚገመግሙበት መንገድ ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር የሚመሳሰል መሆኑን ክፍል ውስጥ ለተማሪዎቻቸው የሚሰጧቸውን ፈተናዎች ሲያወጡ የማጠናቀቂያ ፈተናውን መሰረት አድርገው እንደሆነ ተማሪዎቻቸው በማጠናቀቂያ ፈተናው ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ በማሰብ ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር የሚመሳሰሉ ሞዴል ፈተናዎችን ለተማሪዎቻቸው የሚፈትኗቸው መሆኑን ተማሪዎችን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ለማዘጋጀት የማጠናቀቂያ ፈተናውን መሰረት አድርገው ከፈተናው ጋር ግንኙነት ያላቸውን መለማመጃ ጥያቄዎችን እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

ብዙ ጊዜ በክፍል ውስጥ የትኛውን የአፈታተን ስልት እንደሚተገብሩና ለምን እንደመረጡት ደግሞ አንድ መምህር ዘጠና በመቶ ምርጫ እንደሚፈትኑ ገልፀዋል፡፡ ምክንያታቸውም ክልላዊ ፈተናው ምርጫ ስለሆነ የግድ መዘጋጀት ስለሚኖርባቸው እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ሌሎች ሶስት መምህራን ደግሞ በብዛት ምርጫ እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ ክልላዊ ፈተናው ምርጫ ስለሆነና የምርጫ ጥያቄ የተለያዩ ይዘቶችን ለማካተት ስለሚቻል እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ የምርጫ ጥያቄዎች ለማረም ስለማይቸገሩ እና ተማሪዎችን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ብቁ ለማድረግ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ አንድ መምህር ደግሞ ሁሉንም የአፈታተን ስልቶች እንደሚተገብሩ እና ምክንያታቸውም ተማሪዎች በሁሉም የፈተና አይነቶች ተፈትነው ማለፍ እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

በክፍል ውስጥ ፈተናቸው ብዙ ጊዜ ለየትኛው የቋንቋ ክሂል እና የትምህርት ይዘት የበለጠ ትኩረት እንደሚሰጡና ለምን እንደሚሰጡ ለተጠየቁት ጥያቄዎቸ የሰጡት ምላሽ አንድ መምህር ሁሉንም ለማመጣጠን እንደሚሞክሩ እና የበለጠ ደግሞ ለአንብቦ መረዳት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡አንድ መምህር ለሁሉም ትኩረት እንደሚሰጡ ተናግረዋል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ሁሉንም መገንዘብ ስላለባቸው እና ተጨባጭ የሆነ እውቀት እንዲያገኙ እንደሆነ

ገልፀዋል፡፡ ፈተና ሲዘጋጅ ሁሉንም ይዘቶች የሚያካትት እና የሚዳስስ መሆን ስላለበት ነው፡፡ ሶስት መምህራን ደግሞ ለንባብ ለስነ-ፅሁፍ እና ለሰዋሰው ትኩረት እንደሚሰጡ ተናግረዋል፡፡ ምክንያታቸውም የክልላዊ ፈተናው የበለጠ ሽፍን ስለሚሰጣቸውና ተማሪዎች በቶሎ ስለማይረዷቸው እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

## 4.6 የማጠናቀቂያ ፈተናው የመማሪያ መጽሐፉን ይዘት በማስተማር ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ውጤት ትንተና

የአንደኛ ደረጃ የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን ይዘቱን በማስተማር ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ ለመመርመር የተለያዩ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው መምህራን የሰጡት ምላሽ ቀጥሎ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡ ተማሪዎች የመማሪያ መፅሀፉን ትኩረት ሰጥተው እንዲያነቡት ማሳሰብን በተመለከተ ለቀረበ ጥያቄ አምስቱ መምህራን አናበረታታም በማለት መልሰዋል፡፡ ለዚህም ምክንያታቸውን ሲያስቀምጡ ክልላዊ ፈተናቸው ብዙ ጊዜ ከመማሪያ መፅሀፋቸው ውጭ ስለሚመጣ ከመማሪያ መፅሀፉ ይልቅ ሌሎች አጋዥ መፅሀፍትን እንዲያነቡ የሚያበረታቱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ለምሳሌ፡-አማርኛ (ከ5ኛ-8ኛ)፣መሰረታዊ የአማርኛ መማሪያ አጋዥ መጽሀፍ የሚሉት ናቸው፡፡ የክልላዊ ፈተናው ብዙ ጊዜ ከመማሪያ መፅሀፉ ውጭ ጥያቄዎች ስለሚዘጋጁና መፅሀፉን ትኩረት ሰጥተው ቢያነቡ ፈተናውን መመለስ እንደማይችሉም ተናግረዋል፡፡ እንዲሁም በክልላዊ ፈተናው ውጤታማ እንዲሆኑ ከመማሪያ መፅሀፉ ይልቅ ሌሎች አጋዥ መፅሀፍቶችን ማንበብ ስላለባቸው እንደሆነም ገልፀዋል፡፡ ይህም መምህራን በማጠናቀቂያ ፈተናው ተፅዕኖ ምክንያት ተማሪዎች የመማሪያ መፅሀፉን ትኩረት ሰጥተው እንዲያነቡ የማያሳስቡ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በፅሁፍ መጠይቁም 53.2% ተማሪዎች የመማሪያ መፅሀፉን ለክልላዊ ፈተናው ትኩረት ሰጥተው እንደማያነቡት ገልፀዋል፡፡ ስለሆነም የክልላዊ ፈተናው በመምህራን የትምህርት ይዘት ምርጫ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል ማለት ነው፡፡

ክልላዊ ፈተናው ትኩረት ሰጥቶ የማይዘጋጅባቸውን ከመፅሀፉ ያሉ አንዳንድ ርዕሶችን የሚዘሏቸው መሆኑን በተመለከተ ለቀረበ ጥያቄ አራቱ መምህራን አዎ በማለት መልሰዋል፡፡ ለምሳሌ፡- የማዳመጥ እና የንግግር ክሂል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ በሚከተለው መልኩ ቀርበዋል፡፡ አብዛኞቹ በመማሪያ መፅሀፉ የተካተቱት ይዘቶች በክልላዊ ፈተናው በብዛት ስለማይቀርቡና ተማሪዎች በክልላዊ ፈተናው ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ፈተናው የማይዘጋጅባቸውን ይዘቶች የሚዘሏቸው መሆኑን እና ከተለያዩ

አጋዥ መፅሀፎች ላይ በመመስረት ለክልላዊ ፈተናው ተማሪዎችን ዝግጁ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል፡፡ አንድ መምህር ደግሞ ሁሉንም ርዕሶች እንደሚያስተምሩ ገልፀዋል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ለፈተና ብቻ ሳይሆን ተማሪዎቹ ተጨባጭ የሆነ እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም አባዛኞቹ መምህራን ዋና ትኩረታቸው ተማሪዎችን ለክልላዊ ፈተናው ማብቃት ስለሆነ ቀደም ባሉት ዓመታት ፈተናዎች ውስጥ ተዘውትረው የማይካተቱ ይዘቶች ሲገጥሟቸው እንደሚዘሏቸውና ሌሎች ላይ ይበልጥ ትኩረት እንደሚሰጡ ተናግረዋል፡፡

እንዲሁም ለየትኛው ይዘት እና ክሂል የበለጠ ትኩረት እንደሚሰጡ መምህራን የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ አንድ መምህር ለንባብ፣ ለሰዋሰውና ለጽህፈት የበለጠ ትኩረት እንደሚሰጡ ገልፀው ለንግግር አነስተኛ ትኩረት የሚሰጡ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡ ምክንያታቸው ደግሞ በተማሪዎች ላይ ጎልቶ የሚታየው ችግር የንባብ ፣ የሰዋሰውና የጽህፈት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አራት መምህራን ደግሞ ለንባብ ክሂል የበለጠ ትኩረት የሚሰጡ ሲሆን ምክንያታቸው ደግሞ ማንበብ ሙሉ ስለሚያደርግ እና የክልላዊ ፈተናውም ቢሆን  ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ለንባብ ክሂል የበለጠ ትኩረት ስለሚሰጥ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ንባብ ለሁሉም የቋንቋ ክሂሎች መሰረት ስለሆነና ንባብ በእየ ዓመቱ በክልላዊ ፈተናው ስለማይቀር እንደሆነ ተናግረዋል፡፡  ተማሪዎች የክልላዊ ፈተናውን ለመስራት አንብቦ መረዳትን መለማመድ አለባቸው በማለት ገልፀዋል፡፡ አብዛኞቹ መምህራን በክልላዊ ፈተናው ለሚካተቱ ይዘቶች የተለየ ትኩረት እንደሚሰጡ እና በክልላዊ ፈተናው የማይካተቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን እና ክሂሎችን ዝቅተኛ ትኩረት የሚሰጡ መሆኑን ያመለክታል፡፡መምህራን ሁሉንም የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በእኩል ደረጃ እንደማያስተምሩ እና የክልላዊ ፈተናው የማይዘጋጅባቸውን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ሳያስተምሩ የሚዘሏቸው መሆኑን ያመለክታል፡፡

በሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው ለንባብ ክሂል ፣ ለጽህፈት ክሂል እና ለቃላት በሁለቱ ተከታታይ አመታት በቅደም ተከተል 71.67% ፣ 41.6% ፣ 33.34% ሽፋን ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኞቹ መምህራን ለንበብ ክሂል የበለጠ ትኩረት እንደሚሰጡ ገልፀዋል፡፡ ይህ ደግሞ በክልላዊ ፈተናው ምክንያት የመጣ ነው፡፡

## 4.7 የክፍል ምልከታ ውጤት ትንተና

የክፍል ውስጥ ምልከታ በተመደበው ጊዜ ማለትም በግንቦት እና በሰኔ ወር በ2013 ዓ.ም በቅደም ተከተል ተደርጓል፡፡ ምልከታው በእያንዳንዱ መምህራን ላይ ሁለት ሁለት ጊዜ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ መረጃውን ተጨባጭ ለማድረግ መምህራንን በቪዲዮ ለመቅረፅ ቢታሰብም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ቪዲዮውን መቅዳት አልተቻለም፡፡ ቪዲዮ መቅረፅ ባይቻልም በምልከታው ወቅት መምህራን ያከናወኑት ተግባር ፣ያስተማሩት ይዘት፣ የተጠቀሙት መርጃ መሳሪያ፣ መምህራኑ የተጠቀሙት ጊዜ፣ ተማሪዎች የተጠቀሙት ጊዜ እና ጠቅላላ የግንኙነት ጊዜ ቀጥሎ በሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.7 በክፍል ምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎችን የሚያሳይ ሰንጠረዥ**

| መ | የም.ቀ | የእ.ት.ይ | የተ.ጠ.ማ.ስ | የመ.ተ | መ.የተ.ጊ | የተ.መ | ተ.ቀ.ጊ | ጠ.ጊ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግንቦት 26/2013 ዓ.ም | ተውኔት | መምህር ተኮር | ማስታወሻ ማፃፍ ገለፃ | 35 ደ | አማርኛ (5ኛ-8ኛ) | 5 ደ | 40 ደ |
| ›› | ሰኔ 9/2013 ዓ.ም | የ2010 ዓ.ም የማጠና ቀቂያ ፈተና መስራት | ጥያቄና መልስ ገለፃ | ጥያቄዎችን ማንበብና መልስ መቀበል | 30 ደ | የ2010 ዓ.ም ሽት | 10 ደ | 40 ደ |
| 2 | ሰኔ 16/2013 ዓ.ም | የዘይቤ አይነቶች | መምህር ተኮር | ማስታወሻ ማፃፍ ገለፃ | 36 ደ | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማርያ | 4 ደ | 40 ደ |
| ›› | ሰኔ 8/2013 ዓ.ም | ጥገኛ ሀረጋትን መለየት | ጥያቄና መልስ ገለፃ | ጥያቄዎችን ጥቁር ሰሌዳ ላይ ማስፈርና መልስ መቀበል | 25 ደ | መርጃ መሳሪያ አልተጠቀመ ም | 15 ደ | 40 ደ |
| 3 | ሰኔ 3/2013 ዓ.ም | የቅኔ አፈታት | መምህር ተኮር ገለፃ | ማስታወሻ ማፃፍ ማብራሪያ መስጠት | 35 ደ | የቅኔመማሪ ያ መጽሀፍ | 5 ደ | 40 ደ |
| ›› | ሰኔ 17/2013 ዓ.ም | የ2011 ዓ.ም የማጠና | ጥያቄና መልስ ገለፃ | ጥያቄዎችን መስራት ማብራሪያ | 30 ደ | የ2011 ዓ.ም ሽት | 10 ደ | 40 ደ |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቀቢያ ፈተና | | መስጠት | | | | |
| 4 | ግንቦት 27/2013 ዓ.ም | የቅርብ ሃላፊ ጊዜና የሩቅ ሃላፊ ጊዜ | መምህር ተኮር ገለፃ | ማስታወሻ ማፃፍ ገለፃ | 32 ደ | መሰረታዊ የአማርኛ መማሪያ አጋዥ መጽሀፍ | 8 ደ | 40 ደ |
| ›› | ሰኔ 16/2013 ዓ.ም | ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው ቦታ መጠቀም | ጥያቄና መልስ | ማስታወሻ ጥቁር ሰሌዳ ላይ መፃፍ ማስረዳት | 26 ደ | መሰረታዊ የአማርኛ መማሪያ አጋዥ መጽሀፍ | 14 ደ | 40 ደ |
| 5 | ግንቦት 27/2013 ዓ.ም | ፈሊጣዊ ንግግር | ገለፃ | ማስታወሻ ማፃፍ ገለፃ መስጠት ማስረዳት | 38 ደ | የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መምሪያ | 2 ደ | 40 ደ |
| ›› | ሰኔ 16/2013 ዓ.ም | የ2012 ዓ.ም የማጠና ቀቢያ ፈተና | ገለፃ ጥያቄና መልስ | ጥያቄዎችን ማንበብና መፃፍ ማብራሪያ መስጠት | 32 ደ | የ2012 ዓ.ም ሽት | 8 ደ | 40 ደ |

መግለጫ፡- መ = መምህር ፣የም.ቀ = የምልከታ ቀን ፣የእ.ት.ይ = የእለቱ ትምህርት ይዘት ፣የተጠ.ማ.ሰ = የተጠቀሙት የማስተማር ስነ-ዘዴ ፣ የመ.ተ = የመምህራን ተግባር ፣ መ.የተ.ጊ = መምህራን የተጠቀሙት ጊዜ ፣ የተ.መ = የተጠቀሙት የትምህርት መርጃ መሳሪያ፣ተ.ቀ.ጊ = ተማሪዎች የተጠቀሙት ጊዜ ፣ጠ.ጊ = ጠቅላላ የግንኙነት ጊዜ

ከላይ በሰንጠረዥ 4.7 ስር እንደተመለከተው በሁሉም መምህራን በመጀመሪያ ዙር (ግንቦት ወር ማለቂያ) ላይ በተደረገው ምልከታ ስነ-ጽሁፍንና ሰዋሰውን አስተምረዋል፡፡ በዚህ ምልከታ አራቱ መምህራን በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ስነ-ጽሁፍ ሲያስተምሩ አንድ መምህር ደግሞ ሰዋሰውን አስተምረዋል፡፡ በሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የክልላዊ ፈተናው ለንባብ ፣ ለጽህፈትና ለቃላት የበለጠ ሽፋን ተሰጥቶ ተዘጋጅቷል፡፡ በክፍል ምልከታው ወቀት አብዛኛው መምህራን ስነ-ጽሁፍን ሲያስተምሩ ተስተውሏል፡፡ በጽሁፍ መጠይቁ ደግሞ 51.6% ተማሪዎች በክልላዊ ፈተናው ለሚካተቱ ይዘቶች በክፍል ውስጥ ብዙ ጊዜ እንደሚያጠፉ ገልፀዋል፡፡ ከማስተማሪያ ስነ -ዘዴ አንፃር ደግሞ ሁሉም መምህራን የተጠቀሙት መምህር ተኮር የማስተማር ስነ-ዘዴ ሲሆን በአብዛኛው ለማስተማር የተመደበው ጊዜ በመምህራን የተሸፈነ ነው፡፡ ተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ-ዘዴ አልተገበሩም ፡፡ መምህራን በክልላዊ ፈተናው ተፅዕኖ ምክንያት ከመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያሉትን ይዘቶች ችላ ብለው ከተለያዩ አጋዥ መጽሀፎች ያዘጋጇቸውን ይዘቶች በገለፃ መልክ ለማስተማር ሞክረዋል ፡፡ ለምሳሌ መምህራን የተለያዩ ቅኔያዊ አነጋገሮችን ህብረ ቃል ፣ ሰምና ወርቅ መለየትን ሲያስተምሩ ተማሪዎች እርስ በርስ ተረዳድተው ቅኔዎችን ከመፍታት ይልቅ መምህራን በራሳቸው ቅኔዎችን በገለፃ መልክ አስተምረዋል፡፡ ይህም በክልላዊ ፈተናው የሚካተቱ ይዘቶችን በስፋት ለማስተማር ጊዜ ከመቆጠብ አንፃር ነው ፡፡ በክፍል ምልከታው መምህራን ተማሪዎቻቸውን በክልላዊ ፈተናው እንዲዘጋጁ ሲመክሩ ተስተውሏል፡፡

አዲሱን የመማሪያ መፅሀፍ ለማስተማር የቀረበው የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ እና መምህራን የተከተሉት የማስተማር ስነ-ዘዴ የተለያየ ነው፡፡ አዲሱ የመማሪያ መፅሀፍ ተግባበቦታዊ ቋንቋን የማስተማር ሥነ-ዘዴን እንዲከተሉ የሚጋብዝ ነው:: የመማሪያ መፅሀፍ አላማዎች የተማሪዎችን የተግባቦት ክህሎት በተደጋጋሚ የንባብ፣ የፅህፈት፣ የንግግርና የማዳመጥ ልምምድ ማዳበር ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ በተግባቦት ቋንቋ ማስተማር ስነ-ዘዴ መምህራን የቋንቋ ክህሎችን በጥምረትና በቅንጅት እንዲያስተምሩ ይፈለጋል፡፡ ይሁን እንጂ መምህራን ግን ከዚህ በተለየ የተከተሉት የቆየውን መምህር ተኮር የማስተማር ስነ ዘዴ ነው፡፡ የቋንቋው መምህራን የተለያዩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን ለማስተማር ተመሳሳይ የማስተማሪያ ስነ-ዘዴን ሲከተሉ ተመልክታለች፡፡ የተለያዩና ከማጠናቀቂያ

ፈተናው ጋር ግንኙነት ያላቸውን መፅሀፍት በመርጃ መሳሪያነትም ሲጠቀሙ ተመልክታለች፡፡

በሁለተኛው ዙር በተደረገው ምልከታ ደግሞ የማጠናቀቂያ ፈተናዉ ጊዜ እየቀረበ በመሄዱ ምክንያት ሶስቱ መምህራን በተለያዩ ዓ.ም የተሰጡ ማጠናቀቂያ ፈተናዎችን ለተማሪዎቻቸው ሲሰሩና ሲያሰሩ ተስተውሏል፡፡ በቃለመጠይቁ የተገኘዉ መረጃም ይህንን የሚያጠናቅር ነዉ፡፡ ማለትም መምህራን ተማሪዎቻቸዉ በማጠናቀቂያ ፈተናዉ የተሻለ ዉጤት እንዲያስመዘግቡ ያለፉ አመታት የማጠናቀቂያ ፈተና ወረቀቶችን እንደሚሠሩ ተናግረዋል፡፡ 86.22 % ተማሪዎችም በፅሁፍ መጠይቁ የማጠናቀቂያ ፈተናዉ ከመሰጠቱ አስቀድመዉ ሞዴል ፈተናዎችን እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡ በምልከታዉ ወቅት ጥያቄዎቹ በመምህራን ከተነበቡ ወይም ጥቁር ሰሌዳ ላይ ከተፃፉ በኋላ በተማሪዎች ምላሽ ይሰጥባቸው እና በመምህራኑ በቂ ገለፃና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸው መልሶቹ ይሰራሉ፡፡ አብዛኛው ጊዜም የተሸፈነው በመምህራኑ ሲሆን የተተገበረው የማስተማሪያ ስነ ዘዴም በአባላጫዉ መምህር ተኮር ነበር፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በበተለያዩ አመታት የተሰጡ የማጠናቀቂያ ፈተና ጥያቄዎችን በፍጥነት ለመዳሰስ ነው፡፡ በምልከታው የቀደሙ አመታት የፈተና ወረቀቶች በመርጃ መሳሪያነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

## 4.8.በማጠናቀቂያ ፈተናው የተከሰቱ አዎንታዊና አሉታዊ የወሸባክ አይነቶች

ጥናቱ እንዳመለከተው የተለያዩ አዎንታዊ እና አሉታዊ ተፅዕኖዎች ተከስተዋል፡፡

### 4.8.1.በክልላዊ ፈተናው ተፅዕኖ ምክንያት የተከሰቱ አዎንታዊ ወሸባክ

በዚህ ጥናት በክልላዊ ፈተናው ምክንያት የተለያዩ አዎንታዊ ተፅዕኖዎች የተከሰቱ ሲሆን በመጀመሪያ አማርኛ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት አይነት መሰጠቱ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ትኩረት ሰጥተው እንዲማሩት አድርጓቸዋል፡፡ ሁለተኛው በክልላዊ ፈተናው የተከሰተው አዎንታዊ ወሸባክ ደግሞ ክልላዊ ፈተናው በእየዓመቱ ትኩረት ሰጥቶ የሚዘጋጅባቸው ይዘቶች (ንባብ፣ፅህፈት እና ቃላት ) በመማር ማስተማሩ ክንውን በመምህራን እና ተማሪዎች የተለየ ትኩረት እንዲሰጣቸው ማድረግ መቻሉ ነው፡፡ ይህ ደግሞ መምህራን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ሲሉ እነዚህን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በሰፋት ትኩረት ሰጥተው ስለሚያስተምሩ ተማሪዎች በይዘቶቹ ዙሪያ

ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ሌላው ደግሞ በመማር ማስተማሩ ወቅት ከክልላዊ ፈተናው ጋር ግንኙነት ያላቸው የተለያዩ መለማመጃ ጥያቄዎችን ለተማሪዎቻቸው አዘጋጅተው እንዲሰጡ አበረታቷቸዋል፡፡ ተማሪዎችም ቢሆኑ ከመማሪያ መጽሃፋቸው ውጭ ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ግንኙነት ያላቸውን አጋዥ መጽሀፎች እንዲጠቀሙ አድርጓቸዋል፡፡ ይህም Alderson እና Wall (1993) አዎንታዊ ወሽባክ መምህራን እና ተማሪዎች የመማር እና የማስተማር ግቡን ለማሳካት ተነሳሾች እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ በማለት የገለፁትን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡

## 4.8.2. በክልላዊ ፈተናው ተፅዕኖ ምክንያት የተከሰቱ አሉታዊ ወሽባክ

በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች ክልል በእየ ዓመቱ የሚዘጋጀው አንደኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ የማጠናቀቂያ ፈተና የተለያዩ አሉታዊ ወሽባኮች የታዩበት ሲሆን የመጀመሪያው በመማሪያ መፅሀፉ ላይ ያለው የተወሰኑ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እኩል ሽፋን አለመሰጠቱ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ሁለተኛው በክልላዊ ፈተናው የታየው አሉታዊ ወሽባክ ደግሞ በማጠናቀቂያ ፈተናው የማይካተቱ የትምህርት ይዘቶች እና መልመጃዎች ተማሪዎች ለመማር እና ለመስራት ፍላጎት እንዳይኖራቸው አድርጓቸዋል፡፡ መምህራንም ቢሆኑ እነዚህን ይዘቶችና መለማመጃዎች ትኩረት እንዳይሰጡ አድርጓቸዋል፡፡ ማለትም መምህራንና ተማሪዎች በመማሪያ መፅሀፉ የቀረቡ አላማዎችን ግብ ከማድረስ ይልቅ ለተወሰኑ የትምህርት ይዘቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት በማጠናቀቂያ ፈተናው ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ አድርጓቸዋል፡፡ በተጨማሪም በክልላዊ ፈተናው የታየው አሉታዊ ወሽባክ ደግሞ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን ክፍል ውስጥ የሚያዘጋጁቸው ፈተናዎች ክልላዊ ፈተናውን እንደ ሞዴል የሚጠቀሙ በመሆናቸው የመማሪያ መፅሀፉን መሰረት አድርገው እንዳያዘጋጁ አሉታዊ ተፅዕኖ አድርሶባቸዋል፡፡ ማለትም የቋንቋ ፈተና አላማ የቋንቋውን ትምህርት አላማ ከግብ ለማድረስ የትምህርቱን አላማ ታሳቢ አድርጎ መዘጋጀት ቢኖርበትም በዚህ ጥናት የታየው ግን ከትምህርቱ አላማ ይልቅ ክልላዊ ፈተናውን መሰረት አድርገው እንደሚያዘጋጁ ተስተውሏል፡፡

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በቸሃ ወረዳ በተመረጡ አራት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመምህራንና በተማሪዎች ላይ ያለው ተፅዕኖ መፈተሽ ነው፡፡ ከዚህ ዓብይ ዓላማ የመነጨው የመጀመሪያው ዓላማ የ2011 ዓ.ም እና የ2012 ዓ.ም የ8ኛ ክልላዊ ፈተና ምን ምን ይዘቶችን አካቷል የሚለውን መዳሰስ ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ የተገኘው መረጃ በሁለቱም ተከታታይ ዓመታት ለማንበብ ክሂል ፣ ለመፃፍ እና ለቃላት ከፍተኛ ሽፋን የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ ዓላማ ደግሞ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በተማሪዎች መማር ላይ የአሳደረውን ተፅዕኖ መዳሰስ የሚለው ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ መረጃው ተተንተኖ የተገኘው ውጤት (56.4%) የማጠናቀቂያ ፈተናው ትኩረት በሚያደርግባቸው ይዘቶች ላይ ትኩረት ሰጥተው እንደሚያነቡ ነው፡፡ በመሆኑም Alderson እና Wall (1993) የፈተና ወሽባክ በተማሪዎች መማር ስልት ላይ ተፅዕኖ እንዳለው ያሰፈሩት በጥናቱ ከተገኘው መረጃ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በማጠናቀቂያ ፈተናው ትኩረት በሚያደርግባቸው ይዘቶች ብቻ ትኩረት ሰጥተው የሚያነቡ መሆኑ የማጠናቀቂያ ፈተናው አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሮባቸዋል፡፡ የመማሪያ መፅሀፉ በቂና ለክልላዊ ፈተናው የሚያዘጋጁ መልመጃዎች ያሉት መሆኑንና ለክልላዊ ፈተናው የሚያነቡት መሆኑን በተመለከተ የተገኘው መረጃ (53.2%) በሃሳቡ አንደማይስማሙ ገልፀዋል፡፡ ይህም በቃለ መጠይቅ ከመምህራን ከተገኘው መረጃ ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ (74.18%) ከክልላዊ ፈተናው ጋር ግንኙነት ካላቸው ሰነዶች ጥገኛ እንደሆኑ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ከቀደሙት አመታት የፈተና ወረቀቶች የሞዴል ፈተናዎች ጥገኛ እነደሆኑና ፈተናው በተማሪዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደረ መሆኑን መገነዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በክፍል ውስጥ ምልከታውና በቃለመጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡ ለክልላዊ ፈተናው ምን ዓይነት አጋዥ መጽሀፍቶችን ማንበብ እንዳለባቸው ተፅዕኖ ያሳደረባቸው መሆኑን ለመለየት (51.6%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡ በቃለ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡ Wantanabe (2006) በተማሪዎች መማር ላይ የሚከሰተው የፈተና ተፅዕኖ በመምህራን በክፍል ውስጥ ከሚተገብሩት ጋር የሚመሳሰልና ወደዚያ የሚሄድ ነው በማለት የጠቀሱት ሀሳብ በዚህ ጥናትም ተስተውሏል፡፡ ከቋንቋ ክሂሎች ይልቅ ለሰዋሰዋዊ ይዘቶች ትኩረት ሰጥተው የሚከታተሉ መሆኑን

(51.52%) ያህሉ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ከክሂሎች ይልቅ ለሰዋሰዋዊ ይዘቶች ትኩረት ሰጥተው የሚከታተሉ መሆኑን ነው፡፡ ይህም በቃለ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡በተጨማሪም ሁሉንም የመማሪያ መፅሀፉን ይዘቶች ቢያጠኑ ዝቅተኛ ውጤት የሚያስመዘግቡ መሆኑን በተመለከተ (62.87%) በሃሳቡ እንደማይስማሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ይህም ከሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መረጃ ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡ በቃለ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ጋር አይደጋገፍም፡፡ ክልላዊ ፈተናው በምርጫ መልክ መቅረቡ ጥረት እንዳያደርጉ ያገዳቸው መሆኑን (51.6%) በሀሳቡ እንደማይስማሙ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ክልላዊ ፈተናው በምርጫ መልክ መቅረቡ የቋንቋ ችሎታቸውን ለማሻሻል የማያግዳቸው መሆኑንና በተማሪዎች ላይ አወንታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

ሶስተኛው ዓላማ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በመምህራን የማስተማር ስነ ዘዴና ትግበራቸው ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ መመርመር የሚል ነበር፡፡ ይህን አስመልክቶም መረጃው ተተንትኖ የተገኘው ውጤት (80.63%) ተማሪዎች በክልላዊ ፈተናው ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ የሚያስችሉ የማስተማሪያ ስነ ዘዴዎችን መምህራን እነዲጠቀሙ የሚፈልጉ መሆኑን ነው፡፡ Cheng (2002) በጥናታቸው ውጫዊ (የማጠናቀቂያ) ፈተናዎች መምህራን ለፈተና እንዲያስተምሩ ማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች ለፈተና እንዲማሩ የሚያደርግ እነደሆነ ከገለጡት ሀሳብ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ ይህም ከመምህራን በቃለ መጠይቅ ከተገኘው ሀሳብ ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡ በአጠቃላይ ክልላዊ ፈተናው በመምህራን የማስተማሪያ ስነ ዘዴ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳደረ እንደሆነና መምህራን ቋንቋውን ለማስተማር የሚጠቀሙት የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ለክልላዊ ፈተናው ለስኬት ያበቃቸዋል ብለው የሚያስቡትን ስነ ዘዴ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ሌላው ደግሞ መምህራን ክፍል ውስጥ በክልላዊ ፈተናው የቀረቡ የትምህርት ይዘቶችን ቢያስተምሩ የሚመርጡ መሆኑን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ (61.28%) በሀሳቡ እንደሚስማሙ ገልፀዋል፡፡ Yasin Hajo(2014) ከፍተኛ ውሳኔ የሚወሰንባቸው ፈተናዎች የመምህራን ፣ በተማሪዎች ፣ በወላጆች ፣በስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች እና ፖሊሲ አውጪዎች ላይ የራሳቸውን ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ መምህራንና ተማሪዎች በከፍተኛና በቀጥታ ተፅዕኖ የሚደርስባቸው ናቸው በማለት የጠቀሱት ሀሳብ በዚህ ጥናትም ተስተውሏል፡፡

የጥናቱ አራተኛው  ዝርዝር ዓላማ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በክፍል ውስጥ ፈተና ዝግጅትና ስልት ላይ ያለውን ተፅዕኖ መመርመር የሚል ነበር፡፡ ይህን አስመልክቶ የተገኘው ውጤት መምህራን የክልለዊ ፈተናውን የሚመስሉ ጥየቄዎችን እንደሚያዘጋጁና ተማሪዎች ስለ ማጠናቀቂያ ፈተናው ግንዛቤ እንዲኖራቸው በተለያየ ዓመት ከማጠናቀቂያ ፈተናው የተካቱ ይዘቶችን መሰረት አድርገው በዛው ስልት ጥያቄዎችን እንዲያዘጋጁ እንዳደረጋቸው የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ በአጠቃላይ መምህራን በክፍል ውስጥ በሚያዘጋጇቸው ፈተናዎች ላይ ያለው ተፅዕኖ ምን እንደሚመስል ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረ ተረጋግጧል፡፡ ይህም ከአንጓች (2011) ጥናት ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡

የመጨረሻው የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ በ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ምክንያት የተከሰቱ አወንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖዎች መፈተሽ ነው፡፡ የተገኘው መረጃም እንዳመለከተው የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና አዎንታዊም አሉታዊም ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፤ማጠቃለያ መደምደሚያ እና አስተያየት

## 5.1.ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ  የማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በቸሃ ወረዳ የሚገኙ አራት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች  በመምህራንና በተማሪዎች ላይ ያለው ወሽባክ መፈተሽ ነው፡፡ ይህን አላማ ዳር ለማድረስም ጥናቱ ገላጭ የምርምር ዓይነት ተጠቅሟል፡፡ለዚህም በቸሃ ወረዳ የሚገኙ አራት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 5 መምህራንን በጠቅላይ ናሙና ተመርጠዋል፡፡ እንዲሁም በአራቱም ትምህርት ቤቶች 62 የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በቀላል የእጣ ናሙና ተመርጠዋል፡፡ ከእነዚህም መረጃዎችን ለማግኘት የጽሁፍ መጠይቅ ፣ቃለ መጠይቅ፣ ሰነድ ፍተሻ እና የክፍል ውስጥ ምልከታ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎችን በጽሁፍ መጠይቅ እና በሰነድ ፍተሻ የተገኙት በመጠናዊ በፐርሰት ፣በቃለ መጠይቅና በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኙት ደግሞ ከአላማዎቹ አንፃር በአየጭብጣቸው አይነታዊ በሆነ መልክ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ የተገኙት ውጤቶችም ማብራሪያ ተደርጎባቸዋል፡፡ በሁሉም መንገዶች በተደረጉት የመረጃ ትንተናዎች መሰረትም የተገኙት የምርምሩ ውጤቶች እንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው የጥናቱ አላማ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በተማሪዎች መማር ላይ ያለውን ተፅዕኖ መዳሰስ ነበር፡፡ ይህን አስመልክቶ የተገኘው መረጃ በተማሪዎች መማር ክንውን ላይ አዎናታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ እንዲሁም ክልላዊ ፈተናው በመምህራን የቋንቋ ማስተማር ስነ ዘዴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ በቃለ መጠይቅ ከ5ቱ 4ቱ መረጃ ሰጭዎች ከሰጡት መረጃ ለመረዳት የተቻለው ፈተናው አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረባቸው ነው፡፡ ይህም መምህራን በአመዛኙ ፈተና ተኮር የሆኑ ይዘቶች ናቸው ባሏቸው ላይ ትኩረት እንደሚሰጡ ተስተውሏል፡፡

ሌላው ደግሞ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በክፍል ውስጥ ፈተና ዝግጅትና ስልት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ይህም መምህራን ክልላዊ ፈተናውን የሚመስሉ ጥያቄዎችን እንዲፈትኑ አድርጓቸዋል፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ፈተና በቾሃ ወረዳ የሚገኙ አራት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በመምህራንና በተማሪዎች ላይ ያለው ወሽባክ መፈተሽ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ መረጃዎች ተሰብስበው ተደራጅተው ተተንትነዋል፡፡ የተገኘው ውጤትም ማብራሪያ ተሰጥቶበት ማጠቃለያ ላይም ተደርሷል፡፡ ከዚህ በመነሳትም ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

- የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በተማሪዎች መማር ላይ አወንታዊም አሉታዊም ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ይህም ተማሪዎች ትኩረት ሰጥተው የሚያነቡና የሚከታተሉት በአመዛኙ የክልላዊ ፈተነናው ትኩረት በሚያደርግባቸው ይዘቶች ላይ ብቻ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ሊያደርስ የሚችል ነው፡፡ ይህም ሌሎች የትምህርት ይዘቶችን ችላ እንዲሏቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡ ሌላው የክልላዊ ፈተናው በምርጫ መልክ መቅረቡ በተማሪዎች መማር ላይ ተፅዕኖ እንደ ሌለው የሚያመላክት ነው፡፡
- የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በመምህራን የማስተማር ስነ ዘዴ እና ትግበራቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ይህም መምህራን ቋንቋውን ለማስተማር የሚጠቀሙት የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ተማሪዎችን ለክልላዊ ፈተናው ብቁ የሚያደርጋቸውን እንደሆነ የሚያመላክት ነው፡፡
- የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በክፍል ውስጥ ፈተና ዝግጅትና ስልት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ውጤቱም ተማሪዎች ስለ ማጠናቀቂያ ፈተናው ግንዛቤ እንዲኖራቸው በተለያዩ ዓመታት የተዘጋጁ የሽት ፈተና ይዘቶችን መሰረት አድረገው በዛው ስልት ጥቄዎችን የሚያዘጋጁ መሆኑን ነው፡፡
- የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ለሁሉም የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እኩል ውክልና እንዳልተሰጣቸው የሚያመላክት ነው፡፡
- በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የቀረቡት መረጃዎች በጽሁፍ መጠይቅ ፣ በቃለ መጠይቅና በሰነድ ፍተሻ የተገኘ ውጤት ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 5.3 አስተያየት

በዚህ ጥናት የአማርኛ ቋንቋ ክልላዊ ፈተና በመምህራንና በተማሪዎች ላይ ያለውን ተፅዕኖ ለመፈተሽ የሞከረ ነው፡፡ለዚህም መረጃዎች በጽሁፍ መጠይቅ ፣በቃለ መጠይቅ ፣ በሰነድ ፍተሻ እና በክፍል ውስጥ ምልከታ ተሰብስበዋል፡፡ የተገኘው መረጃ ተተንትኖ ማጠቃለያ ላይ ተደርሷል፡፡ ከዚህ በመነሳትም አጥኚዋ የሚከተሉትን አስተያየቶች ለመጠቆም ሞክራለች፡፡

- መምህራን የክልላዊ ፈተናውን ለመማር ማስተማር ክንውናቸውና ለክፍል ውስጥ ፈተናቸው እንደ ሞዴል ባይጠቀሙና የመማሪያ መጽሀፉን መሰረት አድርገው የክፍል ውስጥ ክንዋኔዎችን ቢተገብሩ
- በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ክንውን መምህራን በመማሪያ መጽሀፉ ለተካተቱ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እና የቋንቋ ክሂሎች እኩል ትኩረት ቢሰጡ እና በክልላዊ ፈተናው በስፋት የማይካተቱትንና ጥያቄ የማይዘጋጅባቸውን ችላ ባይሏቸው
- የቋንቋ መምህራን ተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎችን ለማሳደግ ትኩረት ቢሰጡና ከዚያም ተማሪዎቹን ለክልላዊ ፈተናው ቢያዘጋጇቸው፡፡
- በቃለ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ለማስተዋል እንደተሞከረው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ ምዘና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ይህ ሁኔታ የተማሪዎችን ልዩ የቋንቋ ዝንባሌ ለመመዘንና ለማበልፀግ የማያስችል በመሆኑ የመምህራን የክፍል ውስጥ ምዘና ሁለንተናዊ የተማሪዎችን እድገት ለመመዘን የሚያስችል ሆኖ እንዲገኝ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ቢሰራ
- ክልላዊ ፈተናው ሲዘጋጅ ለሁሉም የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ተመጣጣኝ የሆነ ውክልና ቢሰጠው
- በአጠቃላይ የትምህርት ክፍል ሃላፊዎች ፣ሱፐርቫይዘሮችና የትምህርት ጽህፈት ቤት ባለሙያዎች በመምህራን የማስተማር ሂደት ግንዛቤ ላይ አሉተዊ ተፅዕኖ ማሳደሩን ተረድተው የቋንቋ መምህራን ለተማሪዎች ሁለንተናዊ እድገት ክትትል እና ድጋፍ ቢያደርጉ
- በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በሌሎች ክልሎች እና በተለያዩ አካላት ላይ ያለውን ተፅዕኖ የሚፈትሹ የተለያዩ ጥናቶች ቢደረግ

## ዋቢ መጻህፍት

ስዩም ከበደና ሌሎች፡፡(1994) ፡፡ *አማርኛን የማስተማር ስነ ዘዴ፡፡* አዲስ አበባ፣ትምህርት ሚኒስተር ፡፡

ቅድስተ ማርያም ኮሌጅ፡፡ (1995)፡፡ *የአማርኛ ቋንቋ የማስተማር ስነ ዘዴ፣ ሞጁል የቋንቋ ምንነት፣የቋንቋ ለመዳ ፣የቋንቋ ክሂሎችን ማስተማርና መፈተን(ያልታተመ)፡፡*

ተስፋዬ ሸዋዬ፡፡ (1981)*፡፡ ስነ-ልሳንና ቋንቋን ማስተማር* ፡፡ አዲስ አበባ ፣ (*ያልታተመ*)፡፡

አንጓች ገድሉ፡፡ (2011)፡፡ *የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ ቋንቋ ማጠናቀቂያ ክልላዊ ፈተና በመምህራን የማስተማር ሂደት ላይ ያለው ተጽዕኖ*፡፡ ጎንደር ዩኒቨርሲት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ (*ያልታተመ*) ፡፡

አገኘሁ ተስፋ ፡፡ (2006) ፡፡ *የኢትዮጵያ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ወሽባክ፡፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ (*ያልታተመ*) ፡፡

ያለው እንዳወቅ፡፡ (2009) ፡፡*የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችናአተገባበር (ሶስተኛ እትም)* ፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ::

Alderson J.C. and Wall, D. (1993). *Examining wash back: the srilankan Impacstudy Language testing-10(1)*

Alderson, J.C and Hamp –Lyons, L. (1996).*TOEFL preparation courses: astudy of wash back. Language testing.*

Alderson, J.L. Calap ham C. and Wall D. (2001).*Language test Constraction Evaluation (5th ED).Camridge:* Cambridge University.

Bachman,L.(1990). *Fundamental Considration in languagetesting .Oxford*: OXford University press.

Bachman,L.F. and Palmer,A. (1996). *Language Testing in practice: Design and Developing Useful Language Testes. Oxford*: Oxford University Press.

Bailey, K. (1996).*Wash back in language testing .TOFEL monograph series*.MS 15. Princeton: Educational testing service.

Borich, G. (1996).*Effective teaching methods .prentice-hall*, Inc .Ne Jersey.275 p.

Brown, Douglas. (2007).*Language Assessment Principles and class room practice* .Longman.

Brown, H. (2004). *Language Assessment principles and class room practice*.Sonn Francisco state University.

Brown, J.D (1996). *Testing in Language Programs.New Jersey. Practice Hall*.

Brown, (1980).*Language Assessment Principle and class room practice*.

Callhan, J.F. and Clark.L.H (1988).*Teaching in the middle and secondary schools.Plannin For competence.3rd ed*.New york maemillan Publishing Company.

Cheng, L. (1997).*How does wash back influence testing?* Implications for Hong Kong language and Education.11, 1:38-54

Cheng, L, D.(1998). *The wash back effect of public Examination change on classroom teaching*. Un published doctoral dissertation,university of Hong kong,Hong.kong.

________. (2002).*Wash back of publish examon English teaching* (ERIC Document production servies.No.ED 472167).

________.(2005).*Changing language teaching through language testing awash back* study.Cumbidge:Cup.

Cheng, L.and Curtis, A.(2004).*Wash back or back wash :Areview of the impact Of testing on teaching and learning.*

Harrison. (1989*) Alanguage Testing Hand Book*.London: Macmiliian publishing.

Hopkins,Dk.(1998). *Educational and psychological measurement and evaluation.8th education* ,USA. Allyn and Bacon

Hughes, A. (1989).*Testing for language teachers .Cumbridge*: Cumbridge University press.

Hughes, (2003). *Testing for language teachers. (2nd ed).Cumbridge* : Cup.Language Assessment Quarterly: An international journal http://WWW.tandf on line.com/loihiag20.

Jilani,R.(2009). *Problematizing high school certificate exam in Pakistn*. A wash back perspective .J.the reading matrix. 9(2):175-185

Luxia, Q. (2005). *Stake holders conflicting aims undermine the wash back functioning of high-stakes test.*

Mehrens, W.A and Lehuman, I.J (1974) *standardized test in education .2nd ed.*Michipan State University.

Pan, Y. (2009). *Do test always work*? *The international journal of Educational and Psychological Assessment*.2,74-78.

Pearson,L.(1988).*Tests as levers for change .In chamberlain and R.J.Brum Gartner (Eds) Esp in the class Room*: Practice and evaluation (pp.98-107).

Shih, C, (2009).*How tests change teaching: A model for reference .English teaching: Practice and critique.*

Shohamy, Etal, Donitsa Schmidt, S. and Ferman,I.(1996)'*Test impact revisited :Wash back effect over time'.Language testing*.13/3.298 -317.

Shohamy, Etal. (1992) *beyond proficiency testing adiagnosice feed back testing model assessing forein Language learning modern language journal* 76(4), 513-521.

Simachew, Gashaye.(2012) .*Wash back of the University interance English exam (UEEE) on teachers and Students practices.The case of preparatory schools in Amhara National Regional state Addis Ababa University*:Addis Ababa. (un published Ph.D thesis).

Spart, M.(2005). *Washback and the classroom: the implications for teaching and learning of studies of washback from exam.Language teaching research*.

Taylor, L. (2005).*Wash back and impact ELT journal*.59 (2).

Thorndik, R.L. and Hagen, E. (1977).*Meaurmemt and evaluation in psychology and education*.New York: Join Wiley and Sons, Inc.

Vernon, P, E. (1956).*The measurement of abilities*: London .University of London.

Wantanabe, Y. (2006).*Importance of motivation theories for understanding wash back to the learner.*

Weir C.J. (1990). *Comunicative language testing*. UK.Cambridge University.press http:// WWW---maching-php.

________ (1993).Understand and developing language tests.New York: Prentice Hail international (UK) Ltd

Yasin,Hajo. (2014) .*The wash back effect of Ethiopian General Seconday School Education Certificate English Examination (EGSECEE) on teachers Practice*.Haramaya University. (un published MA thesis).

# አባሪዎች

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ መጠይቅ

**ውድ ተማሪዎች፡-**ይህንን የጽሁፍ መጠይቅ ለመሙላት ስለተባበራችሁኝ አስቀድሜ አመሰግናለሁ፡፡መጠይቁ የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና በመምህራንና በተማሪዎች ላይ ያለውን ተፅዕኖ በተመለከተ ለምርምር የሚውል መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ነው፡፡መረጃው ከምርምር ውጭ ለሆነ ተግባር አይውልም፡፡ በመሆኑም የምትሰጡት መረጃ ለምርምሩ ውጤት ወሳኝ በመሆኑ ተገቢነት ያለውን መረጃ ትሞሉልኝ ዘንድ እጠይቃለሁ፡፡

የመልስ አሰጣጥ ሁኔታ መጠይቁ ትክክል ወይም ስህተት የሚባል መልስ የለውም፡፡ በመሆኑም ከ1-5 ከተሰጡት አማራጮች በአንፃራዊነት የሚገልፃችሁን በትይዩ ባለው ክፍት ቦታ የ X ምልክት ብቻ አድርጉ፡፡

መግለጫ ፡- 1=በጣም አልስማማም 2= አልስማማም 3= ለመወሰን እቸገራለሁ 4 =እስማማለሁ 5 =በጣም እስማማለሁ

| ተ.ቁ | የመጠይቅ ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | **የማጠናቀቂያ ፈተናው በተማሪዎች መማር ላይ እና በመማሪያ መጽሀፉ ዙሪያ የቀረቡ ጥያቄዎች** | | | | | |
| 1 | የማጠናቀቂያ ፈተናው ትኩረት በሚያደርግባቸው ይዘቶች ላይ ብቻ ትኩረት አድርጌ አነባለሁ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | አንዳንድ ይዘቶች በማጠናቀቂያ ፈተናው ባይካተቱም ሁሉንም ይዘቶች አካትቼ ለማንበብ ጥረት አደርጋለሁ | | | | | |
| 3 | በክፍል ውስጥ የምማረው ማጠናቀቂያ ፈተናውን ለመስራት የሚያስችሉ ክሂሎችን እንዲያጎለብቱ የሚያግዙኝን ነው | | | | | |
| 4 | የመማሪያ መጽሀፉ በቂ እና ለክልላዊፈተናው የሚያዘጋጁ መልመጃዎች እንዳሉት አስባለሁ | | | | | |
| 5 | የመማሪያ መጽሀፉ ለክልላዊ ፈተናው ትኩረት ሰጥቶ አላነበውም | | | | | |
| 6 | ከክልላዊ ፈተናው ጋር ግንኙነት ባላቸው የፈተና ሽቶች ላይ ጥገኛ ነኝ(ማለትም ከቀደሙት የፈተና ወረቀቶች ለማጠናቀቂያ ፈተናው ዝግጅት ከሚረዱ የሞዴል ፈተናዎች) | | | | | |
| 7 | ሁሉንም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያሉትን የትምህርት ይዘቶች ባጠና መጥፎ ውጤት ላስመዘግብ እችላለሁ | | | | | |
| 8 | የክልላዊ ፈተናው ምን አይነት አጋዥ መጽሀፎችን ማንበብ እንዳለብኝ ተፅዕኖ አሳድሮብኛል | | | | | |
| 9 | ከቋንቋ ክሂሎች ይልቅ ለሰዋሰዋዊ ይዘቶች ትኩረት ሰጥቼ በክፍል ውስጥ እከታተላለሁ | | | | | |
| 10 | በማጠናቀቂያ ፈተናው ይመጣሉ ብዬ የማስባቸውን መልመጃዎች ትኩረት ሰጥቼ እሰራቸዋለሁ | | | | | |
| 11 | የማጠናቀቂያ ፈተናው በምርጫ መልክ መቅረቡ የቋንቋ ችሎታዬን | | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ለማሻሻል ጥረት እንዳላደርግ ገድቦኛል የሚል ሀሳብ አለኝ | | | | | | |
| | **የማጠናቀቂያ ፈተናው በመምህራን የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴና ትግበራቸው ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄወች** | | | | | | |
| 12 | መምህራችን በማጠናቀቂያ ፈተናው ዙሪያ ጥሩ ውጤት እንድናስመዘግብ የሚያስችሉ የማስተማሪያ ስልቶች ይጠቀማሉ | | | | | | |
| 13 | መምህራችን በማጠናቀቂያ ፈተናው የሚካተቱ የትምህርት ይዘቶችን ለማስተማር የሚያስችሉ ስልቶች ይጠቀማሉ | | | | | | |
| 14 | መምህራችን ክፍል ውስጥ የሚያስተምሩት የቋንቋ ትምህርት ይዘት በማጠናቀቂያ ፈተናው በተደጋጋሚ የቀረቡ ይዘቶችን ነው | | | | | | |
| 15 | መምህራችን ክፈል ውስጥ ንግግር እንድናደርግ ያበረታቱናል | | | | | | |
| 16 | መምህራችን ለማጠናቀቂያ ፈተናው ጥያቄዎችን እንዴት መመለስ እንዳለብን መመሪያ ይሰጡናል | | | | | | |
| 17 | መምህራችን የማስተማር አላማውን ቅደም ተከተል የሚያሲዙት በማጠናቀቂያ ፈተናው ላይ ተመስርተው ነው | | | | | | |
| 18 | መምህራን በማጠናቀቂያ ፈተናው የማይካተቱ የተወሰኑ የትምህርት ይዘቶችን ይዘሏቸዋል | | | | | | |
| 19 | መምህራን አንዳንድ ይዘቶች በማጠናቀቂያ ፈተናው ባይካተቱም ትኩረት ሰጥተው ያስተምራሉ | | | | | | |
| | **የክፍል ውስጥ ተግባራትን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች** | | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | በክፍል ውስጥ የማጠናቀቂያ ፈተና በብዛት ከሚተኮርበት የቋንቋ ትምህርት ይዘት ላይ ብዙ ጊዜ እናጠፋለን | | | | | |
| 21 | የማጠናቀቂያ ፈተናው ከመሰጠቱ በፊት አስቀድሞ ክፍል ውስጥ ሞዴል ፈተናዎችን እንሰራለን | | | | | |
| 22 | በማጠናቀቂያ ፈተናው ምክንያት ለቋንቋው ትምህርት አነስተኛ ትኩረት እንሰጣለን | | | | | |
| 23 | ከማጠናቀቂያ ፈተናው ጋር ግንኙነት የሌላቸውን መልመጃዎችና ተግባራት ችላ እንላቸዋለን | | | | | |

## አባሪ ሁለት

ለመምህራን የቀርቡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

1.በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ይዘቶች ታስተምራለህ/ሽ ?አላስተምርም የምትል/ይ ከሆነ ለምን?

2.አብዝተው የሚጠቀሙት የማስተማር ስነ ዘዴ እና አልፎ አልፎ የሚጠቀሙት የማስተማር ስነ ዘዴ ምን ምን ናቸው? ለምን?

3.በክፍል ውስጥ ምን ምን አይነት የምዘና ስልቶችን ይጠቀማሉ? ምን አይነት ጥያቄዎችን መስጠት ይመርጣሉ ለምን?

4.የማጠናቀቂያ ፈተናው ብዙም የማያተኩርባቸው ከመጽሀፉ ያሉ አንዳንድ ርዕሶችን ትዘላቸዋለህ /ሽ ? አዎ የምትል/ይ ከሆነ ለምን?

5.በመማር ማስተማሩ ወቅት ለየትኛው የቋንቋ ክሂል የበለጠ ትኩረት ትሰጣለህ/ሽ?ለምን ?

6.በክፍል ውስጥ ፈተና ብዙ ጊዜ ለየትኛው የቋንቋ ክሂልና የትምህርት ይዘት የበለጠ ትኩረት ትሰጣለህ/ሽ? ለምን?

7.የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተናው የተግባቦት ቋንቋ ትምህርትን እንዳይተገብሩ ተፅዕኖ ያሳደረባቸው መሆኑንና ያሳደረባቸው ተፅዕኖ ጥቅምና ጉዳት ምንድን ነው?

8.የአንደኛ ደረጃ ማጠናቀቂያ ፈተናው በክፍል ውስጥ ፈተናቸው ላይ የሚያሳድርባቸው ጠፅዕኖ ምንድን ነው?

10. ክልላዊ ፈተናው መምህራን በክፍል ውስጥ በሚያዘጋጁት ፈተና ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ምንድን ነው?

አባሪ ሶስት

የክፍል ምልከታ ቸክሊስት

| መምህራን | የምልከታ ቀን | የእለቱ የትምህርት ይዘት | የተጠቀሙበት የማስተማር ስነ-ዘዴ | የመምህሩ/ሯ ተግባር | መምህሩ/ሯ የተጠቀሙት ጊዜ | የተጠቀሙት መርጃ መሳርያ | ተማሪዎች የተጠቀሙት ጊዜ | ጠቅላላ የግንኙነት ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መምህር 1 | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| መምህር 2 | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| መምህር 3 | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| መምህር 4 | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| መምህር 5 | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |